# የሦስተኛ ክፍል

# የእይታ እና ትወና ጥበባት

# የመምህሩ መምሪያ



ጥቅምት 2014 ዓ/ም





# የሦስተኛ ክፍል

# የእይታ እና ትወና ጥበባት

# የመምህሩ መምሪያ


አዘጋጆች፡- ወርቅነህ ኃ/ሚካኤል
አዉ.ታሩ አራጎ
ምስራቅ ፀሃይ
ታምራት አብራሃም

ሰዓሊ፡- ወርቅነህ ኃ/ሚካኤል

ኤዲተር፡- ፍቃዱ ደጀኔ
ጥራት ተቆጣጣሪ(ፓናሊሰት)፡- ተዋበ ታደሰ
ተክለማርያም ጥላሁን
ቫሊደተር፡- ተስፋዬ እሸቱ
ሲዳማ ስላሴ
ዋንቱሳ ጎንሳ
ይመኙሻል ዮሴፍ
ሀብታሙ ጳውሎስ
ቅድስት ደፋር


ጥቅምት 2014 ዓ/ም

## መግቢያ

የእይታ እና የትውን ጥበባት ትምህርት ለአንድ ሀገር ሕዝብ የሚሰጠው ጥቅም በጣም ከፍተኛ በመሆኑ በመማርና በማስተማር ሂደት ለማህበረሰብ ዕድገት የሚያደርገው አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

ይህ የእይታ እና የትውና ጥበብ ትምህርት በውስጡ ሦስት የትምህርት አይነቶችን (ሙዚቃ ፣ ሥነ- ጥበብ ፣ ተውኔትና ዳንስን) በጥምረት አካቶ የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ሦስት የትምህርት አይነቶች በዘፈቀደ የተቀናጁ ሳይሆን ትምህርቶቹ ያላቸውን የጋራ ባህርያትና የጠበቀ ግንኙነት መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በየክፍለ ትምህርቱ ከመዝሙሮች ጋር የገቡ የሙዚቃ ኖታዎች መምህሩ ዜማውን በሙዚቃ መሳሪያ በመጠቀም የመዝሙሩን ዜማ ለተማሪወች ማስተማር እንዲችል ነው፡፡

ይህ የሦስተኛ ክፍል የእይታ እና የትውና ጥበብ ማስተማሪያ መጽሐፍ በአምስት ምእራፍ የተከፋፈለ ሲሆን፡-

- ❖ ምእራፍ አንድ፡- መለየትና መግለፅ
- ❖ ምእራፍ ሁለት፡- የተግባር ልምምድ
- ❖ ምእራፍ ሦስት፡- ባህላዊ ገለፃዎች
- ❖ ምእራፍ አራት፡- አድናቆት
- ❖ ምእራፍ አምስት፡- የቡድን ትግበራ ናቸው፡፡

በዚህ መፅሐፍ ውስጥ የሙዚቃ ምልክቶችን ( እስከ እሩብ ኖታ እና ሩብ እረፍት ድረስ) ይማራሉ፡፡ መሰረታዊ ቀለማትን እና ቀላል ምስል ፣ የጭውውት ተውኔት ዘዴ ፣ መልዕከት በምስል ፣ በድርጊትና በድመፅ መግለፅን፡፡ ቀላል የሆኑ የሙዚቃ ኖታወች (ምልክቶች ) በመጠቀም በምት መሳሪያዎች መጫወትን ፣ ቤተሰባዊ ክንውኖችን በሙዚቃ ፣ ውዝዋዜ ፣ በማስመሰልና ሚና መጫወትን ይለማመዳሉ፡፡ ንድፍን በመንደፍ ፣ ቀለሞችን

በመቀላቀል ማተምንና መቀባትን ፣ አካባቢያዊ ባህሎችን እና የቀድሞውን እና የአሁኑን ቀለል ያሉ ዕይታዊ ጥበቦችን በማነፃፀር አካባቢያዊ የሆኑ (የሚታወቁ) የሥነ-ጥበብ ድርጊቶችን ይሰራሉ፡፡ በሙዚቃ ፣ በውዝዋዜ ፣ ሚና በመጫወት እና በመተግበር ብሎም በማወዳደር ተማሪዎች ኢትዮጵያዊ እና ማህበረሰብ አቀፍ የሆኑ ሙዚቃዎችን ፣ ስዕሎችን ፣ ውዝዋዜዎችን ፣ ሚና መጫዋትን ፣ ነፃ ንድፍን እና ፎቶ ማንሳትን በማድነቅ እና ባህላዊ ቦታዎችን በመጎብኘት የፅሑፍ ዘገባ እንዲያቀርቡ የሚያግዝ ሆኖ የተዘጋጀ ሲሆን፡፡ ይህ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲማሩበትና ባህላዊ ትውፊቶችን እንዲያሳድጉበት ይህ የመምህሩ መምሪያ የበኩሉን ድርሻ እንደሚያበረክት ከትምህርት ፖሊሲና ሥልጠና ዓላማ አኳያም የታሰበለትን ግብ እንደሚመታ ይታመናል፡፡

ይህ የመምህሩ መምሪያ ከዓላማ ፣ ከይዘት ፣ ከክፍለ ጊዜ ምደባ ፣ አንፃር መምህሩን የሚያሰራ ቢሆንም ተማሪውን የሚያነቃቃ ራሱን ችሎ እንዲሰራ ተማሪ ተኮር አቀራረብን የያዘ ነው፡፡

የክፍለ ጊዜ ሥርጭትን በተመለከተ ትምህርቱ የሚወስደውን ጊዜ ታሳቢ ተደርጎ የተቀመጠ ነው፡፡ በመምሪያው ውስጥም ክትትልና ግምገማ ፣ የማስተማር ስነ-ዘዴንና የማስተማሪያ መሣሪያዎችን አካቶ የያዘ በመሆኑ በዚህ የመምህሩ መምሪያ ውስጥ በዝርዝር የቀረበውን መመሪያ መሠረት በማድረግ እና መምህራን የራሳቸውን ፈጠራ በማከል ትምህርቱን በብቃት ለመወጣት ያስችላቸዋል፡፡

## የትምህርቱ አጠቃ ላይ ዓላማዎች ፡-

ከዚህ የ3ኛ ክፍል ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- የሙዚቃ ምልክቶችን (እስከ እሩብ ኖታ እና ሩብ እረፍት ድረስ) ፣ መሰረታዊ ቀለማትን እና ቀላል ምስልና የጭውውት ተውኔት ዘዴ ፤ መልዕክት በምስል ፣ በድርጊትና በድመፅ ይገልፃሉ፡፡

- ሲጫወቱ ያሳያሉ፡፡
- ቤተሰባዊ ክንውኖችን በሙዚቃ ፣ ውዝዋዜ ፣ በማስመሰልና በመተወን እየተጫወቱ ያሳያሉ፡፡
- ንድፍን በመንደፍ ፣ ቀለሞችን በመቀላቀል ማተምንና መቀባትን ያሳያሉ፡፡
- አካባቢያዊ ባህሎችን እና የቀድሞውን እና የአሁኑን ቀለል ያሉ ዕይታዊ ጥበቦችን ያነፃፅራሉ፡፡
- አካባቢያዊ የሆኑ (የሚታወቁ) የሥነ-ጥበብ ድርጊቶችን በሙዚቃ ፣ በውዝዋዜ ፣ ሚና በመጫወት ይተገብራሉ፡፡
- አካባቢያዊ የሆኑ (የሚታወቁ) የሀገረሰብ ሙዚቃዎችና ውዝዋዜዎችን የቀደሙትን ከአሁኑ ጋራ ያወዳድራሉ፡፡
- ባህላዊ ቦታወችን በመጎብኘት የፅሑፍ ዘገባ ያቀርባሉ፡፡
- ኢትዮጵያዊ እና ማህበረሰብ አቀፍ የሆኑ ሙዚቃዎችን ፣ ስዕሎችን ፣ ውዝዋዜዎችን ፣ ሚና መጫወትን ፣ ነፃ ንድፍን እና ፎቶ ማንሳትን ያደንቃሉ፡፡

## መርጃ መሳሪያወች

- ምቹ የመለማመጃ ክፍል (አዳራሽ)
- የተቀረፁ ድምፆችን የሚያጫውቱ የሙዚቃ ማጫወቻ (ቴፕ ፣ ጅፓስ) ወ.ዘ.ተ
- ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያ
- ስለ ሙዚቃ ኖታ ምልክቶች የተፃፉ መፅሃፍት
- ምቹ የመለማመጃ ክፍል
- እርሳስ ፣ ላፒስ ፣ ማስመሪያ
- መስራች ቀለማት
- ቀለም መቀቢያ (ቡሩሽ)
- ንፁህ ወረቀት

- ከትምህርቱ ጋር የተየያዙ ዜማዎች ወይም መዝሙሮች  የተቀረፀበት ካሴት (ቪዲዮ)
- የተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች

## የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች

- ገለፃ
- ውይይት
- ተግባራዊ ልምምድ
- ጥያቄ እና መልስ
- በዝማሬ የማስተማር ስልት
- አስመስሎ መስራት (መተወን)
- የግል ስራ
- ምልክቶችን (የኖታ እና የእረፍት ) እንዲፅፉ ማድረግ
- በተራ በተራ እየተነሱ እንዲያነቡ ማድረግ
- ንድፍ መስራት

## አጠቃላይ  የክትትልና ምዘና  ዘዴዎች፡-

- የጽሑፍና  የቃል  ጥያቄ
- በተግባር  የሚከናወኑ ሥራዎች ምልከታ
- የቀረቡ ሪፖርቶች
- የተሰሩ ሥራ ውጤቶ  ምልከታ

# ማውጫ

መግቢያ ........ iii
የትምህርቱ አጠቃ ላይ ዓላማዎች ፡- ........ iv
ምዕራፍ አንድ ........ 1
1. መለየት እና መግለፅ ........ 1
1.1. የሙዚቃ ኖታዎች እስከ እሩብ ኖታ እና እሩብ እረፍት ድረስ ........ 2
1.2. መሰረታዊ ቀለማት ........ 15
1.3. ቀለል ያሉ ግለ-ተውኔት እንዲሁም ፎቶ ማንሳትና የዳንስ ስነ-ምግባር ........ 22
ምዕራፍ ሁለት ........ 38
2. የተግባር ልምምድ ........ 38
2.1. ድምፅ፣ሙዚቃ፣ኖታዎች እና የምት ሙዚቃ መሳሪያዎች ........ 40
2.2. ቀላል የሆኑ ዝርግ ቅርጾችን ባለሁለት እና ሦስት አውታር መጠን ቅርጾችን መንደፍ እና ማቅለም ........ 57
2.3. መሰረታዊ ቀለማትን መቀላቀል እና ቀጥታ ህትመት ........ 66
2.3. በተውኔት በተንቀሳቃሽ ምስሎችና ፎቶዎች ያሉ መልዕክቶች ........ 71
ምዕራፍ 3 ........ 86
1. ባህላዊ ገለፃዎች ........ 86
3.1. ባህላዊ ብዝሀነት ባለፈው እና በአሁኑ ጊዜ በእይታና የትውን ጥበባት ሲቃኝ ........ 87
ምዕራፍ አራት ........ 108
4. አድናቆት ........ 108
4.1. ሀገረሰባዊ ጥበባት በትውን እና እይታ ጥበባት በኢተዮጵያ ........ 110
ምዕራፍ አምስት ........ 123
5. የቡድን ተግባር (ግኑኝነት፤ተግባቦት እና ተግባር) ........ 123
5.1. የትውን እና እይታ ጥበባት እርስ በእርስ ያላቸው ግኑኝነት ........ 124

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መለየት እና መግለፅ

*ክፍለ ጊዜ ብዛት (25)*

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች በእይታ እና ትውን ጥበባት ትምህርታቸውን የሙዚቃ የኖታ ምልክቶችን ፣ የእረፍት ምልክቶችን እስከ እሩብ ኖታ እና እሩብ እረፍት ድረስ ያሉ ምልክቶችን ቅርፅ እና አፃፃፍ የሚለዩበት፡፡ መሰረታዊ ቀለማት እነማን እንደሆኑ በስም እና በመልክ የሚለዩበት፡፡ በቀላሉ ፎቶ ማንሳት እና ምጥን ተውኔት ምን እንደሆኑ እንዲረዱ እና እንዲለዩ በማሰብ ለዚህ ክፍል ደረጃ እንዲመጥን ተደርጎ ቀርቧል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች በየንዑስ ክፍለ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱትን ፅሑፎች እና ስዕላዊ መግለጫዎች በሚገባ በማንበብ እና በመገንዘብ ፣ በየንዑስ ክፍለ ትምህርቱ የቀረቡትን የመልመጃ ጥያቄዎች በመስራት የተፈለገውን ውጤት ያመጣሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

## ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

- የሙዚቃ ኖታዎችን እስከ ሩብ ኖታ እና እሩብ እረፍት ድረስ ይለያሉ
- መሰረታዊ ቀለማትን ይለያሉ
- በቀላሉ ፎቶ ማንሳትን እና ምጥን ተውኔትን ይረዳሉ

## የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ

- ህፃናቱ እሰከ ሩብ (1/8 ኛ)ኖታ እና ሩብ (1/8ኛ) እረፍት ድረስ ያሉ ምልክቶችን እንዲለዩ ማድረግ (ምልክቶችን ማስተዋወቅ)

- በምስለ፣ ድምፅ ውስጥ የተካተቱ ምስሎች ፣ እንቅስቃሴወች እና መልዕክቶች
- መስራች ቀለማትን መለየት

## የትምህረት መርጃ መሳሪያዎች

- ምቹ የመለማመጃ ክፍል
- ምስል ፣ ድምፅ እና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻዎች
- ምስል ማሳያዎች

## መመዘኛ

- ምልከታ
- የግል ምላሽ
- የቡድን ምላሽ

# 1.1. የሙዚቃ ኖታዎች እስከ እሩብ ኖታ እና እሩብ እረፍት ድረስ

*የክፍለ ጊዜ ብዛት (9)*

## መግቢያ

በአንድ የንግግር ቋንቋ ውስጥ ያሉ የንግግር ድምፆችን ለመፃፍ ፊደላትን እንደምንጠቀመው ሁሉ በሙዚቃ ውስጥ የምናገኛቸውን ድምፆች ለመፃፍ የምንጠቀምበት ዘዴ ደግሞ ኖታ በመባል ይታወቃል፡፡

ሙዚቃን ቋንቋ ነው የምንለውም እንደማንኛውም ቋንቋ የሚፃፍ ፣ የሚነበብ ፣ የሚደመጥ የራሱ ፊደላት (ኖታዎች) ያሉት በመሆኑ ነው፡፡

## ከዚህ ንዑስ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

- የግማሽ ኖታ እና የግማሽ እረፍት ፣ የሩብ ኖታ እና የሩብ እረፍት ምልክቶችን ቅርፅ መለየት፡፡

- የግማሽ ኖታ እና የግማሽ እረፍት ፣ የሩብ ኖታ እና የሩብ እረፍት ምልክቶችን መፃፍ እና ማንበብ።

## የመማር ማስተማር ስነ-ዘዴ

- ህፃናቱ እስከ ሩብ (1/8 ኛ)ኖታ እና ሩብ (1/8ኛ) እረፍት ድረስ ያሉ ምልክቶችን እንዲለዩ ማድረግ (ምልክቶችን ማስተዋወቅ)
- በምስለ፣ ድምፅ ውስጥ የተካተቱ ምስሎች ፣ እንቅስቃሴወች እና መልዕክቶች

## የትምህርት መርጃ መሳሪያ

- ፍላሽ ካርድ ( ካርዶችን በመቆራረጥ የተሰሩ የኖታ ምልክቶች)
- በትልቁ የተሳሉ የኖታ ምልክቶች( ቻርት)
- ምቹ የመለማመጃ ክፍል

## መመዘኛ

- ምልከታ
- የግል ምላሽ
- የቡድን ምላሽ

***<u>የማነቃቂያ ጥያቄ</u>***

- ከተማሪዎች ልምድና ተሞክሮ በመነሳት አንድ አንድ መሪ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ማቅረብ። ስለ ሙዚቃዊ ምት ተማሪዎች ተራ በተራ እንዲያብራሩ እድል መስጠት።

1) ከአሁን በፊት ስለ ሙዚቃ ኖታዎች የነበራቸውን ግንዛቤ መጠየቅ።
2) የሙዚቃ ኖታዎች ምን አይነት ጥቅም እንዳላቸው መጠየቅ።
3) የሙዚቃ ኖታዎች የምንላቸው ምን እንደሆኑ መጠየቅ እና ምላሽ እንዲሰጡ ማበረታታት።

## 1.1.1. ሙሉ ኖታ እና ሙሉ እረፊት ግማሽ ኖታ እና ግማሽ እረፍት

### 1. ሙሉ ኖታ እና ሙሉ እረፍት

በመጀመሪያ ሙሉ ኖታ ባለ ድመፅ ምልክት አራት ምቶች ያሉት እነደሆነ ማብራራት (መግለፅ)፡፡ በመቀጠልም ሙሉ ኖታ ባለ ድመፅ ምልክት ከግማሽ ኖታ ባለ ድመፅ እና ከሩብ ኖታ ባለ ድመፅ ምልክት ጋር ያለው ልዩነት የቅርፅ ወይም መልክ ብቻ ሳይሆን የአቆጣጠርም ልዩነት እንዳላቸው መግለፅ፡፡

**የመማር ማስተማር ክንዋኔ፡-**

- በትልቁ የተሳሉ የሙዚቃ ኖታ ምልክቶችን ከነዋጋቸው (የጊዜ ቆይታቸው) የሚያሳይ ቻርት ለተማሪዎች በሚታይ ቦታ ማስቀመጥ
- ኖታዎችን እስከ ዕረፍት ምልክታቸው በቻርት በፍላሽ ካርድ በመጠቀም ተማሪዎች የበለጠ እንዲለዮዎቸው ማድረግ፡፡
- ከተማሪዎች ልምድና ተሞክሮ በመነሳት አንድ አንድ መሪ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ማቅረብ፡፡

  ይኸውም፡- ስለ ሙዚቃዊ ምት ተማሪዎች ተራ በተራ እንዲያብራሩ እድል መስጠት፡፡
- በመቀጠልም የሙዚቃ ተነባቢ ፊደላት ምን ተብለው እንደሚጠሩ በመጠየቅ የተማሪዎችን ምላሽ ማዳመጥ፡፡
- ከተማሪዎች አስተያየትና መልስ በመነሳት ከሙሉ እስከ 1/8ኛ ኖታ እና ዕረፍት ምልክታቸው ቅርፃቸውንና አጠቃቀማቸውን በዝርዝር ማስረዳት፡፡
- ተማሪዎቹ በሙሉ ኖታ እና በግማሽ ኖታ መካከል ያለውን የቅርፅ ልዩነት እንዲለዩ ማድረግ፡፡
- ሙሉ ኖታ ዜሮ እንደሚመስል እና ክብ ቅርፅ እንደሆነ በምሳሌ ማስረዳት
- ግማሽ ኖታ ግንድ እና እራስ እንዳለው ማሳየት

➢ ግማሽ ኖታን በሚፅፉበት ጊዜ የግንዱ አቀማመጥ ወደ ላይ ከሆነ ከክብ ራሱ በስተቀኝ ተደርጎ እንደሚፃፍ የግንዱ አቀማመጥ ወደ ታች ከሆነ ደግሞ ከክብ ራሱ በስተግራ እንደሚሆን ማሳየት

➢ ኖታ ምንለው ድመፅን እነደሚተካ እና እረፍት የምንለው ደግሞ ፀጥታን (ድምፅ አልባ) እንደሚተካ (እንደሚወክል) በምሳሌ ማስረዳት፡፡


➢ ተማሪዎቹ ጥቁር ሰሌዳ ላይ እንዲስሉ እድል መስጠት፡፡

***ጠቃሚ መረጃ፡-***

ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ በመጠቀም ተማሪዎች የበለጠ ግንዛቤ እንዲያገኙና የኖታወች ቅርፅ ምን እንደሚመስሉ ማሳየት እና እንዲያውቁ ማድረግ ነው፡፡


| የኖታ ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) | የእረፊት ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) |
|---|---|---|---|---|---|
|  | ሙሉ ኖታ | 4 ምቶች ያሉት ሲሆን<br>በአንድ ትንፋሽ በድመፅ መጫወት |  | ሙሉ እረፊት | 4 ምቶች ያሉት ሲሆን<br>በዝምታ (ድመፅ አልባ) ሆኖ ይቆጠራል |


*ሰንጠረዥ ቁጥር 1*

***ሀ. ሙሉ ኖታ፡-*** ሙሉ ኖታ የምንለው ምልክቱ (  ) ክብ ዜሮ ቅርፅ ሲሆን በአንድ ትንፋሽ አራት ምቶችን ያለማቋረጥ መጫወትን የሚወክል ነው፡፡

***<u>የተግባር ልምምድ -1</u>***

1. ከታች ያለውን የቀስት ምስል በመከተል እጃቸውን በእርጋታ እና በእኩል የጊዜ ቆይታ በማወዛወዝ የኖታ ምልክቱን በትክክል መቁጠር ማለማመድ ፡፡

 አራት ምት ድምፅ መጫወት




አንድ ሙሉ ኖታ ( 𝅝 ) ሁለት ግማሽ (𝅗𝅥 +𝅗𝅥) ኖታወች ተደምረው ከሚሰጡት የጊዜ ቆይታ ጋር እኩል ዋጋ አለው፡፡

ምሳሌ፡- 𝅗𝅥 + 𝅗𝅥 = 𝅝

1&2 3&4 = 1-2-3-4


ሁለት ምት +ሁለት ምት= አራት ምት

## ለ. ሙሉ እረፍት፡- ( 𝄻 )

አራት ምቶች ያሉት ሲሆን በዝምታ (ድመፅ አልባ) ሆኖ ይቆጠራል፡፡ አንድ ሙሉ እረፍት(𝄻)ሁለት ግማሽ እረፍት ( 𝄼 + 𝄼 ) ተደምረው ከሚሰጡት የጊዜ ቆይታ ጋር እኩል ዋጋ አለው፡፡


ምሳሌ፡- 𝄼 + 𝄼 = 𝄻 አራት ምት እረፍት

2 ምት+ 2 ምት = 4 እረፍት 𝄻



*__የተግባር መልመጃ 1__*

1. ከዚህ በታች የተፃፉትን አምስት ባለ ሙሉ ኖታ የድመፅ ምልክት ትክክለኛውን የጊዜ ቆይታቸውን (ዋጋቸውን) በመስጠት ለክፍል ጓደኞቻቸው እነዲያነቡ ያድርጉ፡፡



2. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን አምስት ባለ ሙሉ እረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶችን ለክፍል ጓደኞቻቸው እነዲያነቡ ያድርጉ፡፡



*__መልመጃ 1__*

**ለተዘረዘሩ ጥያቄዎች** መልስ፡-

1. ዝምታ /ፀጥታ/እረፍት
2. ድምፅን
3. አራት /4/ የድምፅ የጊዜ ቆይታ
4. አራት /4/ የዝምታየጊዜ ቆይታ

## 2. ግማሽ ኖታ እና ግማሽ እረፍት

**ሀ. ግማሽ ኖታ፡-** ( 𝅗𝅥 ) በአንድ ትንፋሽ ሁለት ምቶችን ያለማቋረጥ መጫወትን የሚወክል ነው፡፡ ግማሽ ኖታ ( 𝅗𝅥 ) ሁለት ሩብ ኖታወች ( ♩ + ♩ ) ተደምረው ከሚሰጡት የጊዜ ቆይታ ጋር እኩል ዋጋ አለው፡፡


| የኖታ ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) | የእረፈት ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ግማሽ ኖታ | 2 ምቶች ያሉት ሲሆን<br>በአንድ ትንፋሽ መጫወት | | ግማሽ እረፈት | 2 ምቶች ያሉት ሲሆን<br>በዝምታ (ድመፅ አልባ) ሆኖ ይቆጠራል |

*ሰንጠረዥ ቁጥር 2*

***<u>የተግባር ልምምድ -2</u>***

1. ከታች ያለውን የቀስት ምስል በመከተል እጃችሁን በእርጋታ እና በእኩል የጊዜ ቆይታ በማወዛወዝ የኖታ ምልክቱን በትክክል መቁጠር እንዲለማመዱ ያድርጉ።




**ለ. ግማሽ እረፍት** ( ) ሁለት ምቶች ያሉት ሲሆን በዝምታ (ድመፅ አልባ) ሆኖ ይቆጠራል። ግማሽ እረፍት ( ) ሁለት ሩብ እረፍት ( + ) ተደምረው ከሚሰጡት የጊዜ ቆይታ ጋር እኩል ዋጋ አለው።

**<u>ጠቃሚ መረጃ</u>** ፡-ግማሽ ኖታ እና ሩብ ኖታ በሁለት አይነት መንገድ ይፃፋል


I. ግማሽ ኖታ፡- ከክብ ራሱ በስተቀኝ በኩል ሲፃፍ የግንዱን አቀማመጥ የሚያሳይ

II. ግማሽ ኖታ፡- ከክብ ራሱ በስተግራ በኩል ሲፃፍ የግንዱን አቀማመጥ የሚያሳይ

III. ሩብ ኖታ ከክብ ራሱ በስተቀኝ በኩል ሲፃፍ የግንዱን አቀማመጥ የሚያሳይ


IV. ሩብ ኖታ ከክብ ራሱ በስተቀኝ በኩል ሲፃፍ የግንዱን አቀማመጥ የሚያሳይ

- ሩብ ኖታ ባለ ድመፅ ምልክት ስንቆጥር በአንድ ትንፋሽ (ድምፅ ሳይቋረጥ) የቆየው ለአንድ ምት ብቻ እንደሆነ
- ግማሽ ኖታ ባለ ድመፅ ምልክት ስንቆጥር በአንድ ትንፋሽ (ድምፅ ሳይቋረጥ) የቆየው ለሁለት የምት ጊዜ ብቻ እንደሆነ ለተማሪዎች ማስታወስ፡፡



***የተግባር ልምምድ -3***

1. ከላይ በተገለፀው መሰረት ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን አምስት ባለ ግማሽ ኖታ (ባለ ድምፅ) ምልክቶችን በመቁጠር ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችው እንዲያነቡ ማድረግ፡፡




2. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን አምስት ባለ ግማሽ እረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡



## 3. እሩብ ኖታ እና እሩብ እረፍት

በመቀጠል ደግሞ ከታች የተቀመጠውን ሰንጠረዥ በመጠቀም እሩብ ኖታ ፣ እሩብ እረፍት ፣ 1/8ኛ ኖታ እና 1/8ኛ እረፍት ምልክቶችን ቅርፅ እና የጊዜ ቆይታቸውን እንመልከት፡፡


| የኖታ ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) | የእረፈት ምልክት | የምልክቱ ስም | የሚሰጠው ዋጋ (የጊዜ ቆይታ) |
|---|---|---|---|---|---|
|  | ሩብ ኖታ | 1 መት ያለው ሲሆን በአንድ ትንፋሽ በድመፅ መጫወት |  | ሩብ እረፈት | 1 ምት ያለው ሲሆን በዝምታ (ድመፅ አልባ) ሆኖ ይቆጠራል |

*ሰንጠረዥ ቁጥር 3*

**ሀ. እሩብ ኖታ፡-** (  ) አንድ ምት መጫወትን የሚወክል ነው፡፡ ሩብ ኖታ ሁለት 1/8ኛ ኖታወች ተደምረው ከሚሰጡት የጊዜ ቆይታ ጋር እኩል ዋጋ አለው፡፡

*__የተግባር ልምምድ 1__*


1. ከታች ያለውን የቀስት ምስል በመከተል እጃችሁን በእርጋታ እና በእኩል የጊዜ ቆይታ በማወዛወዝ የኖታ ምልክቱን በትክክል መቁጠር ያለማምዱአቸው፡፡




**ለ. ሩብ እረፍት ፡-** (  ) አንድ ምት ድምፅ አልባ መጫወትን የሚወክል ነው፡፡ ሩብ እረፍት ሁለት 1/8ኛ እረፍቶች ተደምረው ከሚሰጡት የጊዜ ቆይታ ጋር እኩል ዋጋ አለው፡፡

*__የተግባር ልምምድ -4__*

1. ከታች ያለውን የቀስት ምስል በመከተል እጃችሁን በእርጋታ እና በእኩል የጊዜ ቆይታ በማወዛወዝ የእረፍት ምልክቱን በትክክል መቁጠር አለማምዱአቸው፡፡



**ጠቃሚ መረጃ ፡-**

የሩብ ፣ ግማሽ እና ሙሉ እረፍት ድምፅ አልባ ምልክቶች ዋጋ ከሩብ ፣ ግማሽ እና ሙሉ ኖታ ባለ ድምፅ ምልክቶች ጋር እኩል የጊዜ ቆይታ (አቆጣጠር) አላቸው፡፡ በዋነኝነት የኖታ እና የእረፍት ምልክቶች አቆጣጠር የሚለዩት የኖታ ምልክቶቹ በድምፅ የሚቆጠሩ ሲሆን የእረፍት ምልክቶቹ ደግሞ ድምፅ አልባ (በዝምታ) የሚቆጠሩ ናቸው፡፡

## የእረፍት ምልክቶች በሙዚቃ ውስጥ


- እንደ ኖታ (ባለ ድምፅ ምልክቶች) ሁሉ የእረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶች በሙዚቃ ውስጥ እጅግ አስፈላጊ እና እጅግ ጠቃሚ ምልክቶች ናቸው፡፡
- የእረፍት ምልክቶች የጊዜ ቆይታና የእረፍት ምልክቶች ስም ቀደም ሲል ከተመለከት ናቸው የኖታ ምልክቶች የጊዜ ቆይታ ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡

የእረፍት ምልክቶች የጊዜ ቆይታና የኖታ ምልክቶች የጊዜ ቆይታ ወይም ጥቅም ካየን አሁን ደግሞ የኖታ ምልክቶችን የእረፍት ምልክቶች  አቆጣጠር ዘዴ በመጠቀም ተማሪወች እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡


***<u>የተግባርመልመጃ -5</u>***

***መመሪያ*** 1፡- የሚከተሉትን የኖታ እና የእረፍት ምልክቶች በመጠቀም ተማሪዎችን በቡድን እና በግል በመጋበዝ ምልክቶችን ማንበብ እንዲለማመዱ ያድርጉ፡፡

1. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን  ሩብ እረፍት ድምፅ አልባ ምልክቶችን በመቁጠር ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያነቡ ያድርጉ፡፡



2. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሩብ ኖታ ባለ ድምፅ ምልክቶችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡



3. ከዚህ በታች የተፃፉትን ሁለት ባለ ሙሉ ኖታ የድመፅ ምልክት ትክክለኛውን የጊዜ ቆይታቸውን (ዋጋቸውን) በመስጠት እንዲያነቡ (እንዲቆጥሩ) ያድርጉ፡፡



4. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሁለት ባለ ሙሉ እረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡



5. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሁለት ባለ ግማሽ ኖታ (ባለ ድምፅ) ምልክቶችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡




6. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሁለት ባለ ግማሽ እረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡



7. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሁለት ባለ ሩብ እረፍት (ድምፅ አልባ) ምልክቶችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡



8. ተገቢውን የጊዜ ቆይታ በመስጠት ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሁለት ባለ ሩብ ኖታ (ባለ ድምፅ) ምልክቶችን እንዲቆጥሩ ያድርጉ፡፡



# 1.2. መሰረታዊ ቀለማት

*የክፍለ ጊዜ ብዛት =8*

## *መግቢያ*

በዚህ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች ስለ አካባቢው የበለጠ እውቀት አድማሳቸውን የሚያሰፉበትና በተፈጥሮአዊና ማህበረሰባዊ ያሉ መስተጋብሮችን የሚከታተሉበት ሥነ-ጥበባዊ ምልከታቸውን የሚያዳብሩበትና ዕውቀትን የሚገበዩበት መንገድ ነው፡፡

በዚህ ትምህርት ውስጥ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ተፈጥሮዎችን ማለትም ወንዞች ፣ መስኮች ፣ ተራሮች ፣ ዕጽዋትና ፣ ደኖች ፣ አራዊትና አእዋፋት እንዲሁም በማህበረሰቡ በየበዓላት ጊዜ የሚለበሱ አልባሳት በቀለማት ፣ ያሸበረቁ መሆናቸውን በመረዳት ስለ ቀለማት ያላቸው ግንዛቤ ሰፋ ያለ ይሆናል፡፡

**ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪወች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- መስራች ቀለማትን መለየት
- መስራች ቀለማትን በስማችው መጥራት
- በአካባቢያቸው የሚገኙ ተፈጥሮአዊና ሰውሰራሽ ቀለም ዓይነቶችን መዘርዘር

**የማስተማር ስነ-ዘዴ**

- መስራች ቀለማትን መለየት
- ስዕሎችን ፣ ፎቶ ማንሻ ቁሶችን ፣ ማሳየት
- ውይይት
- ጥያቀና መልስ

### የትምህረት መርጃ መሳሪያዎች

- ምቹ የመለማመጃ ክፍል
- ምስል፣ ድምፅ እና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻወች
- ምስል ማሳያወች

### መመዘኛ

- ምልከታ
- የግል ምላሽ
- የቡድን ምላሽ
- መረጃ ማከማቻ
- የቤ ትስራ

### <u>ማነቃቂያ ጥያቄ</u>


1. መሰረታዊ ቀለማት ስንል ፣ እነማን እና ምን ዓይነት ናቸው? ይጠይቆቸው።

### ጠቃሚ መረጃ

ከሥነ-ጥበብ ወይም ከእይታ ጥበብ አላባዊያን ማለትም መስመር ፣ ዝርግ የሆኑ ባለሁለት አውታረ መጠን ቅርጾች ፣ ሙሉ የሆኑ ባለ ሦስት አውታረ መጠን ቅርጾች ፣ የልስላሴና ሸካራነት መግለጫ ከሆነው (ቴክስቼር) ፣ የቀለማት ብርሃንና ጥላ መለኪያ (ቫልዩ) እና ቀለም ናቸው። መሥራች ቀለማት በተፈጥሮ ራሰቸውን ችለው ያሉና ከሌሎች ቀለማት ጋር ተቀላቅለው የማይፈጠሩና እንዲሁም ለሌሎች ቀለማት መፈጠር ምክንያት ናቸው። በመሆኑም እርስ በራሳቸው ወይም አንዱ ከሌላው ጋር ተቀላቅለው የሁለተኛና የሦስተኛ ደረጃ ቀለማት የመፈጠር ምክንያት ናቸው።

እነሱም፡-

- ሰማያዊ
- ቢጫ
- ቀይ



*የመሥራች ቀለማት ስዕል ቁጥር 1.1*

***<u>መልመጃ -2</u>***

ከተማሪዎች ልምድና ተሞክሮ በመነሳት አንድ አንድ መሪ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ማቅረብ፡፡

1- ተመሪዎች መሥራች ቀለማት ስንት ናችው?

2- የመስራች ቀለማትን ስማቸውን ዘርዝሩ?


## ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት

መስራች ቀለማት እርስ በርሳቸው ወይንም አንዱ ከሌላው ጋር ሲቀላቀል ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ይመሰርታሉ፡፡


- ሰማያዊ ቀለም ከቢጫ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት አረንጓዴ ቀለም ይሆናል፡፡
- ቀይ ቀለም ከቢጫ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ብርትኩዋንማ ቀለም ይሆናል፡፡
- ሰማያዊ ቀለም ከቀይ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ወይንጠጅ ቀለም ይሆናል፡፡

እነሱም፡-

- ✓አረንጓዴ
- ✓ብርትኳንማ
- ✓ወይንጠጅ



*ስዕል 1.2 አንደኛ ደረጃ ቀለማት እርስበራሳቸው ሲቀላቀሉ ሁለተኛ ደረጃቀለማትን የምገለጽ ቻርት*




*ስዕል 1.3 የአንደኛ እና የሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ቻርት*

***<u>መልመጃ -3</u>***

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡-**

1- ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት የምንላቸውን በስማቸው ገለጹ?

2- ሰማዊ ቀለም ከቀይ ቀለም ጋር ሲቀላቀል ምን ዓይነት ቀለም ይሰጣል?

## ሦስተኛ ደረጃ ቀለማት

- *መስራች ቀለማት ከሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ጋር ሲቀላቀሉ ሦስተኛ ደረጃ ቀለማትን ይሰጣሉ፡፡*

ለምሳሌ፡-

- ቀይ ቀለም ከብርቱካንማ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ቀላ ያለ ብርቱካንማ ቀለም ይሆናል፡፡
- ቢጫ ቀለም ከአረንጓዴ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ቢጫማ አረንጓዴ ቀለም ይሆናል፡፡
- ሰማያዊ ቀለም ከ አረንጓዴ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ሰማያዊ አረንጓዴ ቀለም ይሆናል፡፡

- ቀይ ቀለም ከወይንጠጅ ቀለም ጋር  ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ቀላ ያለ ወይንጠጅ ቀለም ይሆናል፡፡
- ቢጫ ቀለም ብርቱኳንማ ቀለም ጋር  ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ቢጫማ ብርቱኳንማ ቀለም  ይሆናል፡፡
- ሰማያዊ ቀለም ከወይንጠጅ ቀለም ጋር  ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ሰማያዊ ወይንጠጅ ቀለም ይሆናል፡፡

ለምሳሌ፡-

- ቀላ ያለ ብርቱኳንማ ቀለም
- ቢጫማ አረንጓዴ ቀለም
- ሰማያዊ አረንጓዴ ቀለም
- ቀላ ያለ ወይንጠጅ ቀለም
- ቢጫማ ብርቱኳንማ ቀለም
- ሰማያዊማ ወይንጠጅ ቀለም

# የሦስተኛ ደረጃ ቀለማት ቻርት



*ስዕል ቁጥር 1.4 የሦስተኛ ደረጃ ቀለማት ቻርት*

***<u>መልመጃ -4</u>***

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ፡-**

1) የሦስተኛ ደረጃ ቀለማት ዓይነቶችን በስማቸው ዘርዝሩ

2) የሦስተኛ ደረጃ ቀለማት የስንተኛ ደረጃ ቀለማት ውጤቶች ናቸው?

# 1.3. ቀለል ያሉ ግለ-ተውኔት እንዲሁም ፎቶ ማንሳትና የዳንስ ስነ-ምግባር

*የክፍለ ጊዜ ብዛት -8*

## መግቢያ

የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች በአካባቢያቸው የሚያዩዋቸው እና የሚወዷቸውን እንዲሁም የሚያደቁትን ተፈጥሮአዊ እና ባህላዊ የማህበረሰብ ድርጊቶችን ማለትም ሀዘንና ደስታን የሚገልጹብት ክኑዋኔዎችን ቀርጸው (ፎቶ አንስተው) በማስታወሻነት ማስቀመጥ እንዲችሉ ከእይታዊ ጥበብ አንዱ የሆነውን በቀላሉ ፎቶ የማንሳት ዘዴን በመለማመድ ክህሎታቸውን ለማዳበር ይረዳል፡፡

## ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በሁዋላ የሚጠበቅባቸው፡-

- በቀላሉ ፎቶ የማንሳት ዘዴ ምንንት ይገልጻሉ
- ቀላል የፎቶ ማንሻ ምሳሪያዎችን ይለያሉ
- ቀላል የፎቶ ማንሻ ምሳሪያዎችን ያያሉ
- ፎቶ የማንሳት ጠቀመታን ይናገራሉ

## የትምህርቱ መርጃ ምሳሪዎች

- ስዕላዊ መግለጫዎች
- ቀላል ፎቶ ማንሻ ሞደል ቁሶች
- ፎቶ ለማንሳት ምቹ ቦታና ጊዜ

**የማስተማር ስነ-ዘዴ**

- ስዕሎችን ፣
- ፎቶ ማንሻ ቁሶችን ፣ ማሳየት
- ውይይት
- ጥያቀና መልስ

**መመዘኛ**

- ምልከታ
- የግል ምላሽ
- የቡድን ምላሽ
- መረጃ ማከማቻ
- የቤ ትስራ

***<u>የማነቃቂያ ጥያቄ</u>***

ከተማሪዎች ልምድና ተሞክሮ በመነሳት አንድ አንድ መሪ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ማቅረብ፡፡

1. ቀላል ፎቶ የማንሳት ዘዴ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ፎቶ ማንሳት ያለውን ጥቅምና ፋይዳ በየተራ እየተነሱ ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ፡፡

## 1.3.1. በቀላሉ ፎቶ የማንሳት ዘዴ

**ጠቃሚ መረጃ**

በቀላሉ ፎቶ የማነሳት ጥበብ ስንል የሦተኛ ክፍል ተማሪዎቸ በአካባቢያው በቅርበት ከወላጆቻቸው ፎቶ ማንሻ ያላቸውን የእጅ ስልኮችን በመጠቀም በቤታቸው አካባቢ የሚገኙትን አበባዎችን ፣ የቤተሰብ አባላትን ፣ የቤት አንስሳቶችን ፣ ቁሳቁሶችን ፣ ዛፎችን ፣ ተራራዎችን ወዘተ… ማንሳት በቀላሉ ሊለማመዱ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ከአበባ ዓይነቶች አደይ አበባ ፣ ጽገረዳ ፣ የመስቀል አበባ (እንግጫ) ለሎችም ወዘተ…



*ስዕል ቁጥር 1.5 ከአበባ ዓይነቶች ጥቂቶቹ*

ስዕል ቁጥር 1.6 ህጻናት በቀላሉ ፎቶ ማነሳትሚለማመዱባቸው የአበባዓይነቶች



ስዕል ቁጥር 1.6 ህጻናት በቀላሉ ፎቶ ማነሳትሚለማመዱባቸው የአበባዓይነቶች ወይንም ፎቶ፡፡



*ስዕል ቁጥር 1.7 ህጻናት ከወላጆቻቸውና ከጉዋደኞቻቸው ጋር ያላቸውን መስተጋብር የሚሳይ ስዕል ወይንም ፎቶ፡፡*



*ስዕል ቁጥር 1.8 የቤት እንስሳትን የሚገልጹ ስዕሎችና ምስሎች፡*



*ስዕል ቁጥር 1.9 የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች የሚገልጹ ስዕሎችና ምስሎች፡*



*ስዕል ቁጥር 1.10 የዛፎችና ተራራዎችን ማሳየት ወይንም መግለጽ የሚቺሉ ስዕሎችና ምስሎች*

***መለመጃ -5***

1. ፎቶ ማንሻ ቁሳቁሶች ምን ተብለው ይጠራሉ?
2. የፎቶ ማንሻ ጥቅሞችን በቡድን ተወያይታችሁ በጽሁፍ አቅርቡ?

## 1.3.2. ድራማ

ድራማ ከትውን ጥበባት ዘርፎች ማለትም ከስነ-ጽሁፍ ፣ ከስነ-ስእል ፣ ከሙዚቃ ፣ ከውዝዋዜ ፣ ከሰርከስ ትርኢት ፣ ከአስማት ፣ ከኦፔራ ፣ ከፊልም ጥበቦች ወ.ዘ.ተ. ውስጥ የሚካተት ነው፡፡ ድራማ የሰው ልጆችን የእለት ከእለት ገጠመኝ አስመስሎ እየቀዳ የሚከወን ድርጊት ነው፡፡ ታሪክን መነሻ በማድረግ የሚሰራ ነው፡፡ ታሪክ የምንለው መነሻ ሃሳብ ፣ መካከለኛ ሃሳብ እና መጠቅለያ ሃሳብ ያለው ሲሆን ታሪክ ከጊዜ አኳያ ድርጊቶች በቅደም ተከተል ተተንትነው የሚቀመጡበት ክፍል ነው፡፡

***የመወያያ /የማንቂያ/ ጥያቄ***

1. ተማሪዎች ድራማ ማለት ምን ማለት ነዉ?
2. ተማሪዎች አዝናኝና አሳዛኝ ድራማ ምንድን ናቸዉ?

**አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎች**

- ስለ አርዕስቱ እነዲወያዩ ማድረግ
- ገለፃ
- ተግባራትን ሲከውኑ እተከታተሉ ድጋፍ ማድረግ

**የትምህርት ግብዓቶች**

- የመለማማጃ አዳራሽ
- የገፅ ቅቦች
- አልባሳት
- የተለያ ለተውኔት ሚያገለግሉ ቁሳቁሶች

**አጠቃላይ  የክትትልና ግምገማ ዘዴዎች**

- የጽሑፍና  የቃል  ጥያቄ ፣
- በተግባር  የሚከናወኑ ሥራዎች ምልከታ ፣
- የቀረቡ ሪፖርቶች፣
- የተሰሩ  ሥራ  ውጤቶ  ምልከታ

**ጠቃሚ መረጃ፡-**

## ምጥን ድራማ

ድራማ ከትውን ጥበባት ዘርፎች ማለትም ከስነ-ጽሁፍ ፣ ከስነ-ስእል ፣ ከሙዚቃ ፣ ከውዝዋዜ ፣ ከሰርከስ ፣ ትርኢት  ፣ ከአስማት ፣ ከኦፔራ ፣ ከፊልም ጥበቦች ወ.ዘ.ተ. ውስጥ የሚካተትነው፡፡ ድራማ የሰው ልጆችን የእለት ከእለት ገጠመኝ አስመስሎ እየቀዳ የሚከወን ድርግያ ነው፡፡ ታሪክን መነሻ በማድረግ የምሰራ ነው ታሪክ የምንለው መነሻ ሃሳብ ፣ መካከለኛ ሃሳብ እና መጠቅለያ ሃሳብ ያለው ሲሆን ታሪክ ከጊዜ አኳያ ደርጊቶች በቅደም ተከተል ተተንትነው የሚቀመጡበት ክፍል ነው፡፡

**ከዚህ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- ተማሪዎች የድራማን ምንነትን ይረዳሉ፡፡
- ተማሪዎችበድራማዉስጥየምገኙነጥቦችንአዝናኝናአሳዛኝየድራማ(ተዉነት) ዓነቶችንይረዳሉ፡፡

### ድራማ ምንድን ነው? (የድራማ ምንነት)

ድራማ የሚለው ቃል የመጣው ማድረግ ፣ መሥራት ፣ መከወን ፣ ከሚለው ቃል ሲሆን ድራማ ከመባሉ በፍት ጨዋታ በመባል ይታወቅ ነበር፡፡ ጨዋታ የሚለው ቃል ለበርካታ ዘመን ድረስ ለድራማዎች መደበኛ ቃል ሆኖ ያገለገል ነበር ከድራማ ተዋናይ ይልቅ ሠሪ እና ሕንፃው ከቲያትር ቤት ይልቅ የመጫወቻ ቤት ነበር የምባለው፡፡

ድራማ ቲያትር ውስጥ ፣ ወይም በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የተከናወነ ጨዋታ ፣ ኦፔራ ፣ ማይም ፣ ወ.ዘ.ተ. የሚከወነው ክንዋኔዎች ወይም ድርጊቶች በሙሉ ድራማዎች ናቸዉ፡፡ ማመንን ፣ ማስመሰልን ፣ በመተግበር ማስተላለፍን ያካትታል- በመድረኩ ላይ የህይወትን ኑረት የምያሳይ ነው፡፡

ከድራማ ጋር የተቆራኙት ሁለቱ ጭምብሎች አስቂኝ እና አሳዛኝ ድራማ ሁኔታ መካከል ያለውን ባህላዊ አጠቃላይ ክፍፍል ይወክላሉ፡፡ ተውኔቶች ሙሉ በሙሉ አሳዛኝ ወይም አስቂኝ አይደሉም ነገርግን የሁለቱም ቅጾች አካላትን ለማካተት ያቀናብሩ ይህ ተመሳሳይ መሠረታዊ ቅርፅ ባላቸው የተለያዩ ተውኔቶች መካከል እንዲለዩ ይረዳቸዋል፡፡

**አሳዛኝ እና አስቂኝ**



## አሳዛኝ (ትራጄዲ)

ከጥንት ዘመናት ጀምሮ አሳዛኝ ደራማ በጣም የታወቀ የድራማ ዓይነት ነው፡፡ እሱም ከባድ እርምጃን ለማሳየት እና በጨዋታው ውስጥ ከባድ ቃና ይይዛል፡፡ በአሰቃቂ ሁኔታ ውስጥ አስቂኝ እፎይታዎች ሊኖሩ ይችላሉ አሳዛኝ ተውኔቶች ስለ ሰው ሕልውና ተፈጥሮ ፣ ስለ ሥነ ምግባር ወይም ስለ ሰብዓዊ ግንኙነቶች ጉልህ ጉዳዮችን ያነሳሉ፡፡ በጨዋታው ውስጥ ያለው ዋና ገጸ-ባህሪን ተከትለው ብዙውን ጊዜ ተመልካች የገጸ-ባህሪው ስሜት ዉስጥ እንድገቡ እንዲራሩ የሚያደርግ ሰው ነው፡፡ በተለምዶ ባለታሪኩ ጥሩ ወይም ክቡር የሆነ ነገር ለማሳካት እየሞከረ ነው ነገር ግን ይህ ባልተጠበቁ አደጋዎች ተስተጓጉሏል፡፡ አሳዛኝ ሁኔታ ለዚህ ገጸ -ባህሪ ታላቅ ርህራሄ ወይም ርህራሄ ለማመንጨት

የተቀየሰ ነው፡፡ አሳዛኝ ድራማ የተለያዩ አሳዛኝ ክስተቶችን እያስተናገደ በአሰቃቅ ሁነታዎች የተሞላ ነው፡፡

አስቂኝ **(ኮሜዲ)**

አሳዛኝ የሰው ልጅ በምድር ላይ ስለመኖራቸው ትልቅ ጥያቄዎች ቢሆንም ፣ አሳዛኝ በምድር ላይ ምን ያህል የማይረባ ሕይወት ሊሆን እንደሚችል ያሳያል፡፡ ይህ አስደናቂ ቅርፅ እንዲሁ መነሻው በጥንታዊ ግሪክ ውስጥ ነው፡፡ አስቂኝ ብዙውን ጊዜ የሚከሰተው ከተለመደው ወይም ከተጠበቀው ድርጊት አንዳንድ ዓይነት የተለዩ የምያስቁ ክስቶተች የምታይበት ነው፡፡ እንዲሁም አንድ ገጸ-ባህሪ በሚያስገርም ወይም ባልተጠበ ቀሁኔታ ልከዉን ሊከሰት ይችላል፡፡ ኮሜዲ ብዙውን ጊዜ እያዝናና የምያስተምር ነው፡፡ በዋናነት ማዝናናት እና በማሳቅ ክስተቶች ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት ብዙውን ጊዜ ድርጊቱ ሁሉም የምተወነዉ በአዝናኝ ውስጥ ነው፡፡ ለምሳሌ በሙዝ ልጣጭ ላይ በሚንሸራተት ሰው ላይ መሳቅ ቀላል ነው ፣ ግን ግለሰቡ ጀርባውን እንደሰበረ ካወቅን ፣ በጣም አስቂኝ መሆን ያቆማል፡፡ የኮሜዲ የመጨረሻው ዓላማ አድማጮች ወደ ጨዋታው አዝናኝ እንዲገቡ መጋበዝ እና በመድረክ ላይ ካሉ ገጸ-ባህሪዎች ጋር ወይም በሳቅ መሳተፍ ነው፡፡

***<u>መልመጃ -6</u>***

1) ድራማ ምንድን ነው?
   ድራማ ማድረግ ከምለዉ ቃል የመጣ ስሆን ድርጊዎች ክንዋነዎች ድራማ ናቸዉ
2) ድራማ በስንት ይከፈላል ምን ምን ናቸው? አስቂኝና አሳዛኝ ናቸዉ፡፡
3) አሳዛኝ ድራማ ምንድን ነው? አሳዛኝ ድራማ የምያሳዝን አሰቃቂ ሁነታዎቸን የያዘ ነዉ፡፡
4) አስቂኝ ድራማ ምንድን ነው? አስቂኝ እያዝናና የምያስተምር በአስቅኝ ተግባራት የተሞላ ነዉ፡፡

## የምዕራፍ ማጠቃለያ

በአንድ የንግግር ቋንቋ ውስጥ ያሉ የንግግር ድምፆችን ለመፃፍ ፊደላትን እንደምንጠቀመው ሁሉ በሙዚቃ ውስጥ የምናገኛቸውን ድምፆች ለመፃፍ የምንጠቀምበት ዘዴ ደግሞ ኖታ /የኖታ ዘዴ/ በመባል ይታወቃል፡፡

ሙዚቃ ቋንቋ ነው የምንለውም እንደማንኛውም ቋንቋ የሚፃፍ፣ የሚነበብ፣ የሚደመጥ የራሱ ፊደላት (ኖታዎች)ያሉት በመሆኑ ነው፡፡

በምንኖርባት ዓለም ውስጥ ያሉ ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ የራሳቸው ሙዚቃ አላቸው፡፡ ይህም ማለት ያለ ሙዚቃ የሚኖር ማህበረሰብ በምደራችን ውስጥ የለም ማለት ነው፡፡ ሙዚቃ ሰዎች አስተሳሰባቸውን ፣ ፍላጎታቸውን ፣ አኗኗራቸውን ፣ ሃዘናቸውን ፣ ደስታቸውን ወ.ዘ.ተ. ከሚገልፁባቸው መነገዶች ውስጥ አነደኛው የጥበብ ውጤት ሙዚቃ ነው፡፡

የሙዚቃ ኖታ ምልክቶች በሙዚቃ ውስጥ የሚሰጡት ግልጋሎት ከፍተኛ ነው፡፡ እነዚህ የኖታ ምልክቶች በሙዚቃ ውስጥ የምናገኘውን እያንዳንዱን ድምፅ በምን ያህል የጊዜ ቆይታ መጫወት እንዳለብን ወይም የድምፁን የጊዜ እርዝመት መጠን የምንለካባቸው ናቸው፡፡ የኖታ ምልክቶች ድምፅን የሚወክሉልን ሲሆን በተቃራኒው የእረፍት ምልክት የምንላቸው ደግሞ ድምፅ-አልባ /ዝምታን/ የሚወክሉ ናቸው፡፡

በሙዚቃ ውስጥ ያለውን የድምፅ ቆይታ የሚወክሉ በርካታ የሙዚቃ ኖታ ምልክቶችን በሙዚቃ ውስጥ እናገኛለን፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

**መመሪያ 1 ከዚህ በታች ለተዘረዘሩ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ**

1) በሙዚቃ ውስጥ ኖታ የምንለው /የኖታ ምልክት/ ምንን ይወክልልናል?
2) በሙዚቃ ውስጥ እረፍት የምንለው /የእረፍት ምልክት/ ምንን ይወክልልናል?
3) በሙዚቃ ውስጥ የምናገኛቸውን ድምፆች ለመፃፍ የምንጠቀምበት ዘዴ ምን በመባል ይታወቃል?
4) በሙዚቃ ውስጥ ሙሉ ኖታ ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
5) በሙዚቃ ውስጥ ግማሽ ኖታ ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
6) በሙዚቃ ውስጥ ሩብ ኖታ ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
7) በሙዚቃ ውስጥ ሙሉ እረፍት ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
8) በሙዚቃ ውስጥ ሩብ እረፍት ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
9) በሙዚቃ ውስጥ ግማሽ እረፍት ስንት ምቶች /የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት?
10) ግማሽ ኖታ እና ሩብ ኖታ ስንት አይነት አፃፃፍ አላቸው?

**መመሪያ 2 ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተክክለኛውን መልስ ምረጡ**

1) ከሚከተሉት መስራች ቀለም ያልሆነው የቱነው

ሀ/ወይንጠጅ ሐ/ሰማያዊ

ለ/ቢጫ መ/ቀይ

2) ከቤታችን በቀላሉ ፎቶ ለማንሳት የምንችላቸው ነገሮች

ሀ/ የቤትውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ሐ/የወላጆቻቸውን

ለ/የቤትእንስሳት መ/ሁሉም

3) ከሚከተሉት ውስጥ ሁለተኛ ደረጃ ቀለም የቱነው

ሀ/ቀይ ሐ/ብርትኳንማ

ለ/ ሰማያዊ መ/ቢጫ

4) ሦስተኛ ደረጃ ቀለማት ያልሆነው

ሀ/ቀላያለ ብርትኳንማ ሐ/ቢጫማአረንጓዴ

ለ/ቀይ መ/ሰማያዊወይነጠጅ

5) ለቀለሞች መቀላቀያ የሚገለግሉ ቁሳቁሶች

ሀ/ወንፊት ሐ/ቀለም መቀቢያ(ብሩሽ)

ለ/ዝርግ ሳሀን መ/ውሃ

**መመሪያ 3 የሚከተሉት ጥያቄዎችን እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ**

1)ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት በተፈጥሮ ራሳቸውን ችለው ያሉ ቀለማት ናቸው፡፡

2) ቢጫ ቀለም ከሰማያዊቀለምጋር ሲቀላቀል ብርተኳንማ ቀለምይሰጣል፡፡

3) የእጅ ስልኮች ቀላል ፎቶ ማንሻ ሆነው ማገልገል ይችላሉ፡፡

**በመመሪያ 1 ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ**

1) ድምፅን
2) ዝምታን/ድምፅ አልባ/
3) በሙዚቃ ውስጥ የምናገኛቸውን ድምፆች ለመፃፍ የምንጠቀምበት ዘዴ ምን በመባል ይታወቃል?
4) አራት ምቶች /የድምፅ የጊዜ ቆይታዎች/አሉት
5) ሁለት ምቶች /የድምፅ የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት
6) አንድ ምት /የድምፅ የጊዜ ቆይታ/ አለው
7) አራት ምቶች / ድምፅ አልባ የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት
8) አንድ ምት /ድምፅ አልባ የጊዜ ቆይታ/ አለው
9) ሁለት ምቶች /ድምፅ አልባ የጊዜ ቆይታዎች/ አሉት
10) ሁለት አይነት

**በመመሪያ 2 ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ**

1) ሀ/ወይንጠጅ
2) መ/ሁሉም
3) ሐ/ብርትኳንማ
4) ለ/ቀይ
5) ሀ/ወንፊት

**በመመሪያ 2 ለተጠየቁየእውነትሀሰትጥያቄዎችመልስ**

1)እውነት
2)ሐሰት
3)እውነት

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የተግባር ልምምድ

*የክፍለ ጊዜ ብዛት =27*

### መግቢያ

በዚህ ክፍለ ትምህርት ዉስጥ የሦስተኛ ክልል ተማሪዎች የእይታ ጥበብንና ሥነ-ዉበትን መግለጽ ከሚያስችላቸው እና እውቀት የሚያገኙበት አንዱና ዋነኛው መንገድ የተግባር ልምምድ ነው፡፡ የተግባር ልምምድ ተማሪዎች ማንኛውንም የጽንሰ ሀሳብ ትምህርቶች ወደ ተግባር ልምምድ ማድረግ የሚያስችላቸው የተመቻቸ ጊዜ እና አመቺ ቦታ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ የተግባር ልምምድ ተማሪዎች አካባቢያቸው ከሚገኙ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሠራሽ ቁሶች (ግብዓቶች ) የራሳቸውን ፈጠራዊ ገለጻዎችን ለማዳበር ያስቸላቸዋል፡፡

**ከክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- የኖታ ምልክቶችን (ጊዜ እና የእረፍት ምልክቶችን የማንበብ እና የመፃፍ ልምምድ ያደረጋሉ፡፡
- በድምፅ ከማንበብ በተጨማሪ የምት ሙዚቃ መሳሪዎችን በመጠቀም ኖታዎችን ያነባሉ፡፡
- በሙዚቃ ፣ በውዝዋዜ እና በማስመሰል ትውን ጥበባት አርአያ /ምሳሌ/ የሚሆን ቤተሰብ የሚያደረጋቸውን ተግባራት እንዲያቀርቡ ማደረግ፡፡
- መሳል ፣ መንደፍ ፣ ቀለማትን መቀላቀል ማተም እና ማቅለም

### መርጃ መሳሪያወች

- ምቹ የመለማመጃ ክፍል (አዳራሽ)

- የተቀረፁ ድምፆችን የሚያጫውቱ የሙዚቃ ማጫወቻ (ቴፕ ፣ ጅፓስ) ወ.ዘ.ተ
- ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያ
- ስለ ሙዚቃ ኖታ ምልክቶች የተፃፉ መፅሃፍት
- ምቹ የመለማመጃ ክፍል
- እርሳስ ፣ ላፒስ ፣ ማስመሪያ
- መስራች ቀለማት ፣ ቀለም መቀቢያ (ቡርሽ)
- ንፁህ ወረቀት
- ከትምህርቱ ጋር የተየያዙ ዜማዎች ወይም መዝሙሮች የተቀረፀበት ካሴት ( ቪዲዮ)፣
- የተለያዩ የሙዚቃ መሣሪያዎች

**የማስተማሪያ መንገድ**

- ገለፃ
- ውይይት
- ተግባራዊ ልምምድ
- ጥያቄ እና መልስ
- በዝማሬ የማስተማር ስልት
- አስመስሎ መስራት (መተወን)
- የግል ስራ
- ምልክቶችን (የኖታ እና የእረፍት ) እንዲፅፉ ማድረግ
- በተራ በተራ እየተነሱ እንዲያነቡ ማድረግ
- ንድፍ መስራት

**አጠቃላይ የክትትልና ምዘና ዘዴዎች፡-**

- የጽሑፍና የቃል ጥያቄ ፣
- በተግባር የሚከናወኑ ሥራዎች ምልከታ ፣

- የቀረቡ ሪፖርቶች፣
- የተሰሩ ሥራ ውጤቶ ምልከታ

## 2.1. ድምፅ፣ሙዚቃ፣ኖታዎች እና የምት ሙዚቃ መሳሪያዎች

*የክፍለ ጊዜ ብዛት =9*

### መግቢያ

ሙዚቃ ማለት ድምፆችን በማዋቀር (በማቀናጀት) ለጆሮ በሚስብ እና በሚማርክ መልኩ ሀሳባችንን እና ስሜታችንን የምንገልፅበት አንደኛው የጥበብ መንገድ መሆኑ በክፍል አንድ ትምህርታችን ላይ ገልፀን ነበር፡፡

ይህንን ስንል አንድን ሙዚቃ ለመስራት በዋነኝነት ከሚያስፈልጉ ነገሮች አንደኛው ድምፅ ነው፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥም ድምፅ በሙዚቃ ውስጥ ያለውን ሚና እና ድምፅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንማራለን፡፡

ከዚህ ምእራፍ በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

- በሙዚቃ ውስጥ ድምፅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይረዳሉ፡፡
- ስንት አይነት የድምፅ አይነቶች እንዳሉ ይለያሉ፡፡
- የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን አሰራር ይረዳሉ
- በአካባቢያቸው ያሉ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን በቡድን በመሆን ይሰራሉ፡፡
- በአካባቢያቸው ያሉ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ ያወቃሉ፡፡
- በምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ኖታዎችን ያነባሉ፡፡

**አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎች፡-**

- የቡድን ውይይት
- ሪፖርት ማቅረብ
- ሙከራ
- ጥያቄና መልስ

- የግል ጥናት
- ምርምር  ማድረግ
- ትረካ
- ልምድ  ያላቸውን ሰዎች መጋበዝ
- ቢዲዮ  ማሳየት
- ሰርቶ ማሰራት፡፡

**የትምህርት  ግብዓቶች**

- ምቹ የመለማመጃ ክፍል
- ድምፅ እና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻወች፣
- አካባቢያዊየምት ሙዚቃ  መሳሪያወች ወ.ዘ.ተ
- ምስልና ድመፅ ማጫወቻወች (ማሳያወች)
- ከትምህርቱ  ጋር  የተየያዙ  ዜማዎች  ወይም  መዝሙሮች የተቀረፀበት  ካሴት ( ቪዲዮ)፣
- ለትምህርቱ  የሚያስፈልጉ ቻርቶች ፣
- የተለያዮ የባህል እና ዘመናዊ የሙዚቃ  መሣሪያዎች፡፡
- ክራር ከበሮ

**አጠቃላይ  የክትትልና ግምገማ ዘዴዎች**

- የጽሑፍና  የቃል  ጥያቄ ፣
- በተግባር  የሚከናወኑ ሥራዎች ምልከታ ፣
- የቀረቡ ሪፖርቶች፣
- የተሰሩ  ሥራ  ውጤቶ  ምልከታ፡፡

***<u>የመወያያ /የማንቂያ/ ጥያቄ</u>***

1. ተማሪዎች በአካባቢያቸው ከሚታወቅ የባህል ሙዚቃ በጋራ እንዲያዜሙ እና እንዲወዛወዙ ያድርጉ፡፡
2. ተማሪዎችን ስለ ድምፅ ምንነት ይጠይቁ፡፡

### 2.1.1 ድምፅ

ድምፅ ማለት ማንኛውም ነገር (ቁስ) በሚርገበገብበት ወይም እርስ በእርስ በሚጋጭበት ጊዜ የሚፈጠር በጆሮ ልንሰማው የምንችለው ነገር ሁሉ ድምፅ ይባላል፡፡

ድምፅ ማለት ማንኛውም ነገር (ቁስ) በሚረገበገብበት ወይም እርስ በእርስ በሚጋጭበት ጊዜ የሚፈጠር በጆሮ ልንሰማው የምንችለው ነገር እንደሆነ ከላይ በመግቢያችን ገልፀን ነበር፡፡ በእርግብግብታ የሚፈጠሩ ድምፆች ተርገብጋቢው ነገር (ቁስ) አየሩን በሚቀዝፍበት ጊዜ የሚፈጠር ድምፅ ሲሆን ይህም ረዘም ላለ ጊዜ ወይንም እርግብግብታው እስኪቆም ድረስ ድምፁን ልንሰማው እንችላለን፡፡

ለምሳሌ የተወጠረ የክራርን ገመድ (ሲር) ስበን ስንለቀው ገመዱ ወዲያውኑ ድምፅ ይፈጥርልናል፡፡ የድምፅ ቆይታውም የገመዱ ርግብግብታ እስከሚያቆም ድረስ ልንሰማው እንችላለን፡፡

## ከንዑስ ክፍለ ትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ድምጽ ማለት ምን እንደሆነ እንዲያውቁ ማድረግ
- ድምጽ እንዴት እነደሚፈጠር ይረዳሉ
- ድምጽ የሚፈጥሩ መሳሪያዎችን በአካባቢቸው ከወዳደቁ ቁሶች እነዲሰሩ ማድረግ፡፡

**የመማር ማስተማር ክንዋኔ**

- ልጆች በቡድን በአካባቢያችሁ የወዳደቁ ጣውላወችን ጂማት(ሲር) በመጠቀም፡፡
- ክራር እንዲሰሩ ማድረግ፡፡
- ከጅማቱ ድምፅ እንዴት እንደሚወጣ ሞክሮ ማሳየት፡፡
- ድምፅ እንዴት እንደሚፈጠር በቅርባቸው ያለ ነገርን በመጠቀም ማሳየት፡፡

- ስንት አይነት ድምፆች እንዳሉ ማብራራት፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

በማጋጨት እና በማፋጨት የሚፈጠሩ ድምፆች በአብዛኛው ጊዜ የድምፅ ቆይታቸው የሚወሰነው እንደ መሳሪያዎቹ (እንደሚጋጩት ነገሮች) የመርገብገብ ባህሪ ነው፡፡

ተማሪዎች አካባቢያቸው ላይ ባሉ ነገሮች እንዲማሩ ማደረግ ተገቢ ነው፡፡

ይህ ማለት ለምሳሌ በእስክርቢቷችሁ የተቀመጣችሁበትን ወንበር ወይም ጠረጴዛ ብትመቱ ወድያውኑ ድምፅ ሲፈጠር ትሰማላችሁ ነገር ግን በእስክርቢቷችሁ የመታችሁት ጠረጴዛ ወይም ወንበር የተሰራው ከእንጨት ከሆነ የድምፅ ቆይታው በጣመ አጭር ጊዜ ብቻ ሲሆን በአንፃሩ ከብረት (ቆርቆሮ) ከሆነ ደግሞ የድምፅ ቆይታው ከቀድሞው ሊረዝም ይችላል፡፡ ሌላው መጠኑ ከፍ ባለ የቀለም ቆርቆሮ ወይም ውስጡ ክፍት በሆነ ገበታ መሰል ነገር ላይ ቆዳ ወጥረን በዱላ ብንመታው ድምፁን ረዘም ላለ የጊዜ ቆይታ ልንሰማው እንችላለን፡፡ ይህም ሚሆነው የቀለም ቆርቆሮው ወይም ገበታው ውስጡ ክፍት በመሆኑ የቆዳውን እርግብግብታ ይዞ ስለሚቆይ ነው፡፡


## ሀ. የድምፅ አፈጣጠር

ድምፅ የሚፈጠረው ማንኛውም ነገር (ቁስ) በሚረገበገብበት ወይም እርስ በእርስ በሚጋጭበት ጊዜ የሚፈጠር በጆሮ ልንሰማው የምንችለው ነገር እንደሆነ ከላይ በመግቢያችን ገልፀን ነበር፡፡ በእርግብግብታ የሚፈጠሩ ድምፆች ተርገብጋቢው ነገር (ቁስ) አየሩን በሚቀዝፍበት ጊዜ የሚፈጠር ድምፅ ሲሆን ይህም ረዘም ላለ ጊዜ ወይንም እርግብግብታው እሰኪቆም ድረስ ድምፁን ልንሰማው እንችላለን፡፡

ለምሳሌ፡- የተወጠረ የክራርን ገመድ (ሲር) ስበን ስንለቀው ገመዱ ወዲያውኑ ድምፅ ይፈጥርልናል፡፡ የድምፅ ቆይታውም የገመዱ ርግብግብታ እስከሚያቆም ድረስ ልንሰማው እንችላለን፡፡



ስዕል ቁጥር 2.1 ሾንካ




*ስዕል ቁጥር 2.2 ክራር*

***<u>የተግባር መልመጃ 1</u>***

1፡ ልጆች በአካባቢያችሁ የወዳደቁ ጣውላወችን ጂማት (ሲር) በመጠቀም ክራር አዘጋጅታችሁ ከጅማቱ ድምፅ እንዴት እንደሚወጣ ለማየት ሞክሩ፡፡

በማጋጨት እና በማፋጨት የሚፈጠሩ ድምፆች፡- በማጋጨት እና በማፋጨት የሚፈጠሩ ድምፆች ደግሞ በአብዛኛው ጊዜ የድምፅ ቆይታቸው የሚወሰነው እንደ መሳሪያዎቹ( እነደሚጋጩት ነገሮች) የመርገብገብ ባህሪ ነው፡፡

ይህ ማለት ለምሳሌ በእስክርቢቷችሁ የተቀመጣችሁበትን ወንወበር ወይም ጠረጴዛ ብትመቱ ወድያውኑ ድምፅ ሲፈጠር ትሰማላችሁ ነገር ግን በእስክረቢቷችሁ የመታችሁት ጠረጴዛ ወይም ወንበር የተሰራው ከእንጨት ከሆነ የድምፅ ቆይታው በጣመ አጭር ጊዜ ብቻ ሲሆን በአንፃሩ ከብረት (ቆርቆሮ) ከሆነ ደግሞ የድምፅ ቆይታው ከቀድሞው ሊረዝም ይችላል፡፡ ሌላው መጠኑ ከፍ ባለ የቀለም ቆርቆሮ ወይም ውስጡ ክፍት በሆነ ገበታ መሰል ነገር ላይ ቆዳ ወጥረን በዱላ ብንመታው ድምፁን ረዘም ላለ የጊዜ ቆይታ ልንሰማው እንችላለን፡፡ ይህም ሚሆነው የቀለም ቆርቆሮው ወይም ገበታው ውስጡ ክፍት በመሆኑ የቆዳውን እርግብግብታ ይዞ ስለሚቆይ ነው፡፡

***<u>የተግባር መልመጃ -2</u>***

1. መምህራችሁ በሚያሳዩአችሁ መሰረት በአካባቢያችሁ የሚገኙ ቁሶችን በመጠቀም ከበሮ ወይም አታሞ መስራትን ተለማመዱ፡፡



ስዕል ቁጥር 2.3 ቲምባ



ስዕል ቁጥር 2.4 ነጋሪት



*ስዕል ቁጥር 2.5 አታሞ*

## ለ. የድምፅ አይነቶች

በቀደመው ትምህረታችን ድምፆች እንዴት እንደሚፈጠሩ አይተናል በመቀጠል ደግሞ የድምፅ አይነቶች ስንት እንደሆኑ እና ምን አይነት ባህሪ እንዳላቸው እናያለን፡፡

ድምፆች ባላቸው ባህሪያት መደበኛ (ሙዚቃዊ) እና መደበኛ ያልሆኑ (ኢ-ሙዚቃዊ) ብለን በሁለት እንከፍላቸዋለን፡፡

## ሐ. ሙዚቃዊ (መደበኛ) ድምፆች

መደበኛ (ሙዚቃዊ) ድምፆች የምንላቸው ውስን በሆነ የድምፅ እርግብግብታ የሚፈጠሩ እና ለጆሮ የማይረብሹ ወይም የሚመቹ ሙዚቃዊ ድምፆች ሲሆኑ እነዚህንም ድምፆች በአካባቢያችንም ሆነ በአለማችን ለሙዚቃ ስራ ምንጠቀምባቸው ናቸው፡፡

በአብዛኛው የአለማችን ሙዚቀኞች የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያም እነዚህን መደበኛ ሙዚቃዊ ድምፆች የሚያወጡ ወይም በነዚህ ድምፆች

የተቃኙ ናቸው፡፡ ለምሳሌ የፒያኖ/ ኪቦርድ/ ቁለፎችን በመጫን የምንሰማቸው ድምፆች መደበኛ የሆኑ እና የእየራሳቸው ስሞች ያሉቸው ናቸው፡፡

## መ. ሙዚቃዊ ያልሆኑ (ኢ-መደበኛ) ድምፆች

መደበኛ ያልሆኑ (ኢ-ሙዚቃዊ) ድምፆች የምንላቸው ደግሞ ባልተወሰነ በሆነ የድምፅ እርግብግብታ የሚፈጠሩ እና ለጆሮ የሚሰቀጥጡ ሸካራ ድምፆች ሲሆኑ የሚረብሹና የሚያውኩ ድምፆች ናቸው፡፡

ለምሳሌ ያህል በገበያ አካባቢ የምንሰማቸው ሁካታዎች ፣ ከመጠን በላይ ጮክ ብሎ የሚሰማ ሙዚቃ ፣ የትራፊክ መጨናነቅ በሚበዛበት አካባቢ የሚሰሙ የመኪና ጥሩንባዎች ወ.ዘ.ተ… ሲሆኑ፡፡ እነዚህ አይነት ድምፆች አዕምሮን የሚረብሹ እና ጤናንም የሚጎዱ ድምፆች ናቸው፡፡

### ***<u>መልመጃ -1</u>***

1. ድምፅ እንዴት ይፈጠራል
2. ስንት አይነት ድምፆች አሉ
3. ሙዚቃዊ/መደበኛ/ ድምጽ የምንላቸው ምን አይነት ድምፆችን ነው
4. ኢ-ሙዚቃዊ/ኢ-መደበኛ/ ድምጽ የምንላቸው ምን አይነት ድምፆችን ነው

### ጠቋሚ ነጥብ

ሙዚቃዊ/መደበኛ/ ድምጽ የምንላቸው ምን አይነት ድምፆች እንደሆኑ የተቀረፁ ድምፆችን ለተማሪዎች በማሰማት እንዲለዩ ማድረግ፡፡

ኢ-ሙዚቃዊ /ኢ-መደበኛ/ ድምጽ የምንላቸው ምን አይነት ድምፆች እንደሆኑ የተቀረፁ ድምፆችን ለተማሪዎች በማሰማት እንዲለዩ ማድረግ፡፡

## 2.1.2. የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች

የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች የምንላቸው የተወጠሩ ቆዳዎችን በምንመታበት ጊዜ ድምፅ የሚፈጥሩ የሙዚቃ መሳሪያዎች ሲሆኑ እነዚህንም አይነት የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች በተለያዩ የሃገራችን ክፍሎች

እናገኛቸዋለን፡፡ ቲምባ ፣ ከበሮ ፣ አታሞ ፣ ድቤ ፣ ነጋሪት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት በሃገራችን ከሚገኙ የምት የሙዚቃ መሳሪዎች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡

**ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን ባህሪ ይረዳሉ
- የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን አሰራር ይረዳሉ
- በአካባቢያቸው ያሉ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን በቡድን በመሆን ይሰራሉ፡፡
- በአካባቢያቸው ያሉ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ ያወቃሉ

*__የአእምሮ ማነቃቂያ፡-__*

1. ከበርካታ የብሄረሰብ ሙዚቃዎች ውስጥ ለወዝዋዜ አመች የሆነውን ዜማ መረጦ እንዲጫወቱ ማድረግ፡፡
2. ተማሪዎች ስለ ሙዚቃ ቀድሞ ያላቸውን ግንዛቤ ስለ ሙዚቃ ምንነት በመጠየቅ ምላሽ ይውሰዱ፡፡

**የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ**

- ምቹ የመለማመጃ ክፍል
- ድምፅ እና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻወች፣
- አካባቢያዊየምት ሙዚቃ  መሳሪያወች ወ.ዘ.ተ
- ምስልና ድመፅ ማጫወቻወች (ማሳያወች)
- ከትምህርቱ ጋር የተየያዙ ዜማዎች ወይም መዝሙሮች የተቀረፀበት  ካሴት ( ቪዲዮ)፣
- ለትምሀርቱ  የሚያስፈልጉ ቻርቶች ፣
- የተለያዮ የባህል እና ዘመናዊ የሙዚቃ መሣሪያዎች፡፡
- ክራር ከበሮ

**የመማር ማስተማር ክንዋኔ**

- ሙከራ፣
- ጥያቄና መልስ፣
- የግል ጥናት፣
- ምርምር ማድረግ፣

**አጠቃላይ የክትትልና ግምገማ ዘዴዎች፡-**

- የጽሑፍና የቃል ጥያቄ ፣
- በተግባር የሚከናወኑ ሥራዎች ምልከታ

***ጠቃሚ መረጃዎች***

**ትምባ** ፡- የምት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ከከበሮ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በቀደመው ዘመን ትምባ የሚዘጋጀው ቀለል ያለ እንጨት ውስጡ ተቦረቡሮ ቆዳ በመሸፈን ነበር ዛሬ ላይ በእንጨት ምትክ የገረወይና ቆርቆሮ ጥቅም ለትምባ ምቹ እንዲሆን በከርሞሃ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ተቀጥቅጦ ይዘጋጅና ቆዳ በጠፈር ይወጠርበታል፡፡ ትምባ በአንዳንድ የደቡብ ኢተዮጰያ አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎችበሐዘንም ሆነ በደስታ ጊዜ ጭፈራን ለማድመቅ የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡

**አታሞ፡-**በጉራጌ ብሄረሰብ ውስጥ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች በብዛት የሚጠቀሙበት የሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን መጠኑ አነስተኛ የሆነ እና በእጅ የሚመታ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ አታሞ ከሸክላ( ድስት) ላይ የፍየል ወይም የበግ ቆዳን በመወጠር ሊሰራ ይችላል፡፡



*ስዕል 2.6 አታሞ*

***ነጋሪት፡-*** የምት የሙዚቃ መሳሪዎች ከምንላቸው ውስጥ የሚካተት ሲሆን በቀድሞ ጊዜ ነገስታት አዋጅ ለማወጅ እና በጦርነት ወቅት መልዕክት ለማስተላለፍ ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ነጋሪት ከእነጨት እና ከቆዳ የሚሰራ ሲሆን ውስጡ ከተቦረቦረ እና ገበታ ከመሰለ አንጨት ላይ ቆዳ በመወጠር የሚሰራ የምት ተሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ የምንጫወተውም አጭር እና ከወደ ቂጡ ቆልመም ባለ ዱላ በገበታው ላይ የተወጠረውን ቆዳ በመምታት ነው፡፡




*ስዕል 2.7 ነጋሪት*

**ከበሮ፡-** የኢተዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቄሶች የሚጠቀሙበት የምት ሙዚቃ መሳሪያ ሲሆን ከሌሎች የሀገራችን የምት ሙዚቃ መሳሪያወች የሚለየው መጠኑ ከፍያለ እና የስሊንደር ቅርፅ ያለዉ በሁለቱም በኩል በእጅ በመምታት ሁለት የተለያዩ ድመፆችን ማውጣት የሚችል የምት የሙዚቃ መሳሪያ በመሆኑ ነው፡፡ ከበሮ ከእንጨት ፣ ከነሀስ ፣ ከመዳብ እና ከብር ሊሰራ ይችላል፡፡ እንጨቱ ከተቦረቦረ እና ውስጡ ክፍት ከሆነ በኂላ በሁለቱም አቅጣጫ ቆዳ በመወጠር የሚሰራ የምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ሰፊውን የከበሮ ክፍል በቀኝ እጃችን ጠባቡን የከበሮ ክፍል ደግሞ በግራ እጃችን በመምታት ከበሮን መጫወት እንችላለን፡፡



*ስዕል 2.8 ከበሮ*

**ሀላካ፡-** ሃላካ የሚባለው ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያ እንጨቶችን በአጭሩ በመቆራረጥ እና በመጥረብ ለእጅ አያያዝ እንዲመች ተደርጎ የሚዘጋጅ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ሃላካ በእጅ ከማጨብጨብ ይልቅ በሃላካ ማጨብጨብ ጨዋታን ስለሚያደምቅ ጭብጨባን የሚተካ ነው ይላሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ሃላካ ከጭብጨባ ጋር ግንኙነት የለውም እንደ አንድ የሙዚቃ መሳሪያ ዘፈኖችን ለማጀብ የሚውልና የራሱ የዘፈኑም መጠሪያ ነው የሚሉ አሉ፡፡ በተለይም ሐረ ሐላካ የተሰኘው ዜማ ማጀቢያ ሃላካ የተባለው የምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡



*ስዕል 2.9* ሃላካ (*ጋይሌ*)

***<u>መልመጃ 2</u>***

1) *ሀለካ የምንለው የሙዚቃ መሳሪያ ከምን ይሰራል?*
2) በቀድሞ ጊዜ ነገስታት አዋጅ ለማወጅ እና በጦርነት ወቅት መልዕክት ለማስተላለፍ ይጠቀሙበት የነበር የምት የሙዚቃ መሳሪያ ምን ይባላል?
3) ከከበሮ ጋር ተመሳሳይነት ያለው የምት የሙዚቃ መሳሪያ ማን ይባላል?

## 2.1.4 በምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ኖታዎችን ማንበብ

በባህል የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ታግዞ ኖታዎችን ማንበብ ማለት በመጀመሪያው የትምህርታችን ምዕራፍ ላይ ያሉትን የኖታ እና እረፍት ምልክቶች ላ..ላ.. ወይም ታ..ታ.. እያልን በአፋችን እናንባቸው የነበሩትን በምት የሙዚቃ መሳሪያ ተክቶ ማንበብ ማለታችን ነው።

**ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- በአካባቢያቸው ባሉ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሙዚቃ ኖታዎችን ማንበብ ማስቻል፡፡

**አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎች**

- በባህል የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ታግዞ ኖታዎችን ማንበብ እነዲችሉ ማድረግ
- በመጀመሪያው የትምህርታችን ምዕራፍ ላይ ያሉትን የኖታ እና እረፍት ምልክቶች ላ..ላ.. ወይም ታ..ታ.. እያልን በአፋችን እናነባቸው የነበሩትን በምት የሙዚቃ መሳሪያ ተክቶ ማንበብ ማለታችን ነው፡፡
- ተማሪወችን ልምምድ እንዲሰሩ ማገዝ፡፡


**የትምህርት ግብዓቶች**

- ምቹ የመለማመጃ ክፍል
- ድምፅ እና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻወች፣
- አካባቢያዊየምት ሙዚቃ  መሳሪያወች ወ.ዘ.ተ
- ምስልና ድመፅ ማጫወቻወች (ማሳያወች)
- ለትምሀርቱ  የሚያስፈልጉ ቻርቶች ፣
- የተለያዮ የባህል እና ዘመናዊ የሙዚቃ  መሣሪያዎች፡፡
- ክራር ከበሮ

**አጠቃላይ የክትትልና ግምገማ ዘዴዎች**

- በተግባር  የሚከናወኑ ሥራዎች ምልከታ

ከዚህ በታች የተቀመጡትን የኖታ እና የእረፍት ምልክቶች ለማንበብ ሞክሩ



## 2.2. ቀላል የሆኑ ዝርግ ቅርጾችን ባለሁለት እና ሦስት አውታር መጠን ቅርጾችን መንደፍ እና ማቅለም

*የክፍለ ጊዜ ብዛት =6*

### መግቢያ

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች የእይታ ጥበብንና ሥነ-ውበትን መግለጽ ከሚያስችላቸው እና እውቀት የሚያገኙበት አንዱና ዋነኛው መንገድ የተግባር ልምምድ ነው፡፡ የተግባር ልምምድ ተማሪዎች ማንኛውንም የጽንሰ ሀሳብ ትምህርቶች ወደ ተግባር ልምምድ ማድረግ የሚያስችላቸው የተመቻቸ ጊዜ እና አመቺ ቦታ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ የተግባር ልምምድ ተማሪዎች አካባቢያቸው ከሚገኙ ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሠራሽ ቁሶች (ግብዓቶች) የራሳቸውን ፈጠራዊ ገለጻዎችን ለማዳበር ያስቸላቸዋል፡፡

**ይህንን ትምህርት ካጠናቀቁ በሁዋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጥቶች፡-**

- ቀላል የሆኑ ዝርግ ቅርጾች ወይም ባለ ሁለት አውታረመጠን ቅርጾን ይለያሉ
- ባለ ሁለትና ባለ ሦስት አውታረመጠን ቅርጾች ሊዩነት ይገልጻሉ
- ባለ ሦስት አውታረመጠን ቅርጾችን ቀለም ይቀባሉ
- የቀጥታ ህትመትን በማትም ይተገብራሉ

## የትምህረቱ መርጃ መሣሪዎች

- ምቹ የሆኑ የመለማመጃ ክፈሎች
- እርሳስ ፣ ላጲስ ፣ ማስመሪያ ፣ ንጹህ ወረቀት
- መስራች ቀለማት ፣ ማለትም ሰማያዊ ፣ ቢጫ ፣ ቀይ ፣ ቀለማት ናቸው፡፡
- ለቀለማት መቀለማት መቀቢያ የሚያገለግሉ በቀላሉ ከአካባቢያችን የሚገኙ በዶሮ ላባዎች
- በከብት ጭራ እና በቃጫ በሚሰሩ መቀቢዎች
- ቀለማትን ማቅጠኛ ውሃ
- ቀለማትን መቀላቀያ (ፓለት)

***<u>ማንቂያ (መሪ ተግባራት)</u>***

1. ተማሪዎች ባካባቢቸው ካዩዋቸውና ስለሚያውቁዋቸው ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሠራሽ የቀለም ዓይነቶች በቡድን ተወያተው በዝርዝር እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

**የመማር ማስተማር ክንውኖች**

- ስዕልን ማሳል( ንድፍ ማሰራት)
- ቀለማትን እንዲቀላቅሉ ማድረግ
- ቀጥታ ህትመትን እንዲያትሙ ማድረግ

- ቀለማትን እነዲያቀልሙ ማዘዝ

**ክትትልና ግምገማ (ምዘና)**

- ምልከታ
- የቡድን ሥራ
- የቤት ሥራ
- የቃል ጥያቀ
- መረጃ ማከማቻ

**ጠቃሚ መረጃዎች**


ቀላል የሆኑ ባለ ሁለት አውታረ መጠን ያላቸው ዝርግ ቅርጾች ማለት በእይታዊ ጥበብ ውስጥ የሚገለጹት በውጫዊ መስመር አማካኝነት ነው፡፡ ባለ ሁለት አውታረመጠን ያላቸው ዝርግ ቅርጾች በተፈጥሮአዊና በሰው ሰራሽ ቀሶችን በነጠላ መሥመር በመንደፍ የሚገለጽበት መንገድ ወይም ዘዴ ነው፡፡

## 2.2.1. ባለ ሁለት አውታረ መጠን ያላቸው ዝርግ ቅርጾችን መሳል እና ማቅለም

ቀላል የሆኑ ባለ ሁለት አውታረ መጠን ያላቸው ዝርግ ቅርጾች ማለት በእይታዊ ጥበብ ውስጥ የሚገለጹት በውጫዊ መስመር አማካኝነት ነው፡፡ ባለ ሁለት አውታረመጠን ያላቸው ዝርግ ቅርጾች በተፈጥሮአዊና በሰው ሰራሽ ቁሶችን በነጠላ መሥመር በመንደፍ የሚገለጽበት መንገድ ወይም ዘደ ነው፡፡

ለምሳሌ ፡- ተፈጥሮአዊ የሆኑ ባለ ሁለት አውታረ መጠን ቅርጾች (ዝርግ ቅርጾች) ስንል የበትና የዱር እንስሳት ፣ ተራሮች ፣ ዛፎች(ደኖች) ፣ ወንዞችና ዳመና ፣ ክዋክብት ጸሐይና ጨረቃ በእየታዊ ጥበብ ሲገለጹ ያለምንም ብርሃንና ጥላ በነጠላ መስመር (በንድፍ) ቢቻ ይሠራሉ፡፡


ለምሳሌ- ተፈጥሮአዊ የሆኑ ባለ ሁለት አውታረ መጠን ቅርጾች ቀላል የሆኑ ባለ ሁለት አውታረ መጠን ያላቸው ዝርግ ቅርጾች ማለት በእይታዊ ጥበብ ውስጥ የሚገለጹት በውጫዊ መስመር አማካኝነት ነው፡፡ ባለ ሁለት አውታረመጠን ያላቸው ዝርግ ቅርጾች በተፈጥሮአዊና በሰው ሰራሽ ቁሶችን በነጠላ መሥመር በመንደፍ የሚገለጽበት መንገድ ወይም ዘዴ ነው፡፡



*ስዕል 2.10 ተፈጥሮአዊ የሆኑ ባለ ሁለትአውታረመጠን ዝርግ ቅርጾች፡፡*

## ለሁለት አውታረመጠን ዝርግ ቅርጽ የቤት ውስጥ መገልገያ

## ቁሳቁስ



*ስዕል 2.11: ሰው ሠራሽ ባለሁለት አውታረመጠን ዝርግ ቅርጾች*

**ስዕል ባለሁለት አውታረ መጠን ዝርግ ቅርጽ የቤት አይነቶች**



*ስዕል 2.12 ስዕል ባለሁለት አውታረ መጠን ዝርግ ቅርጽ*

### 2.2.2. ባለሦስት አውታረ መጠን ቅርጾችን መሳል እና ማቅለም

ባለሦስት አውታረመጠን ቅርጽ ወይም ቁስ ማለት የሚዳሰስ ፣ የሚጨበጥ እንዲሁም ርዝመት ፣ ስፋት ፣ ጥልቀት ያለው አካል ማለት ነው፡፡ ባለሦስት አውታረመጠን ቅርጽ ብርሃን ባረፈበት ተቃራኒ አቅጣጫ ጥላ በመፈጠሩ ሙሉ ቀርጽ መሆኑን ይገልጻል፡፡


ለምሳሌ፡- ተፈጥሮአዊ የሆኑ ባለሦስት አውታረመጠን ቅርጽ ስንልየበትና የዱር እንስሳት ፣ ተራሮች ፣ ዛፎች(ደኖች) ፣ ወንዞችና ዳመና ፣ ክዋክብት ፣ ጸሐይና ጨረቃ በእየታዊ ጥበብ ሲገለጹ ከነሙሉነታቸው ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ተፈጥሮአዊ የሆኑ ባለ ሦስት አውታረ መጠን ቅርጾች ስእላዊ መግለጫዎች፡፡



*ስዕል 2.13 ተፈጥሮአዊ የሆኑ ባለ ሦስት አውታረ መጠን ቅርጾች ስእላዊ መግለጫዎች*

እንደዚሁም ሰውሰራሽ የሆኑ ባለሦስት እውታረመጠን ቅርጾች ሙሉ ሲሆኑ ርዝመት ፤ ስፋትና ጥልቀት ያላቸው ናችው በላያቸው ላይ ብርሃን ባረፈበት ተቃራኒ አቅጣጫ ጥላ ሲወድቅ ሙሉ ቅርጽ ወይም በለሦስት አውታረ መጠን ቀርጽ ይባላሉ፡፡



*ስዕል 2.14 ሰው ሰራሽ ባለሦስት አውታረመጠን ቅርጾች*



*ስዕል 2.15 የጋሞ አካበቢ ባህላዊ የቤት ዓይነቶች*

**ተፈጥሮኣዊ ሰው ሠራሽ ባለ ሦስት አውታረ መጠን ቅረጾች**



*ስዕል 2.16 ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ ባለ ሦስት አውታረ መጠን ቅርፆች*

**መልመጃ** 4

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ**

1. ባለሁለት አውታረመጠን ስንል ምንማለት ነው?
2. ባለሦስትና ባለሁለት አውታረ መጠን ቅርጾች አድነትና ልዩነት ግለጹ?
3. ባለሦስት አውታረመጠን ስእሎችን እቤታችሁ ስላችሁ እንድትመጡ?

## 2.3. መሰረታዊ ቀለማትን መቀላቀል እና ቀጥታ ህትመት

*የክፍለ ጊዜ ብዛት =12*

### መግቢያ

በዚህ ንዑስ ክ/ትምህርት መሰረታዊ ቀለማትን በመቀላቀል ሌሎች ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን እንዴት ማግኘት እንደምንችል እና ቀጥታ ህትመት ሲባል ምን እንደሆነ ከእይታ ጥበባት ማለትም ከቀለምቅብ ፣ ከንድፍ (በእርሳስ የሚሳል ስእል) ቅርጻ ቅርጽ ከመሳሰሉት አንፃር ተማሪዎችምይህንን የጥበብ ዓይነት በቀላሉ ባካባቢያቸው ከሚገኙ ቁሶች መስራትና መተግበር መማር ያስችላቸዋል፡፡ በመሆኑም ይህንን በተግባር ለመከወን የሚስችላቸው አመቺ የመስሪያ ቦታና ቁሳቁሶች ያስፈልጋቸዋል፡፡

ተማሪዎች መስራች ቀለማትን እርስ በእርሳቸው ሲቀላቅሉ ሌላ ቀለም ማለትም ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ማግኘት ሲቻል እንደገና አንደኛ (መስራች) ቀለማት ከሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ጋር ሲቀላቀሉ ሦስተኛ ደረጃ ከለማትን እንደሚፈጥሩ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ቀለማትን በመቀላቀል የምናገኘው ውጤት ለምንስለው ስዕል ትክክለኛውን መልክ አስመስለን መቀባት እንድንችል ይረዳናል ለዚህም ተግባር የሚረዱን ከአካባቢያችን በቀላሉ ከሚገኙ ቀሶች መቀቢየዎችን (ቡርሾችን) መስራት ከሚቻልባቸው መካከል ለሚሳሌ ከዶሮ ላባ ፣ ከእንስሳት ጸጉር(ጭራ) ፣ ከቃጫ ወዘተ... ከመሳሰሉት ቀጭን አንጨት ወይንም ጭራሮ ጫፍላይ በማሰር ለቀለም መቀቢያነት መጠቀም ይቻላል፡፡

**ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ የሚጠበቅባቸው፡-**

- መሰረታዊ ቀለማትን በመቀላቀል ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ይፈጥራሉ
- ህትመትን ከሌሎች የእይታ ጥበባት ማነጻጸር፡፡
- ለቀጥታ ህትመት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን መለየት፡፡
- ለቀጥታ ህትመት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፡፡
- ከአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች ቀጥታ ህትመትን ማተም፡፡

***የማንቂያ ጥያቄ*** :-

1. ተማሪዎች ህትመት ማለት እና ቀጥታ ህትመት ልዩነታቸውን በቡድን ተወያይታችሁ በጽሁፍ አቅርቡ፡፡
2. ህትመት ከሌሎች የእይታ ጥበብ ዓይነቶች በምን እንደምለይ ተወያዩ፡፡

**ጠቃሚ መረጃ**

መስራች ቀለማት እርስ በርሳቸው ወይንም አንዱ ከለላው ጋር ስቀላቀል ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ይመሰርታሉ፡፡


- ሰማያዊ ቀለም ከቢጫ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት አረንጓዴ ቀለም ይሆናል፡፡
- -ቀይ ቀለምከቢጫ ቀለም ጋርሲቀላቀል የሚገኘው ውጤትብርትኩዋንማ ቀለም ይሆናል፡፡
- ሰማያዊ ቀለም ከቀይ ቀለምጋርሲቀላቀል የሚገኘው ውጤትወይንጠጅ ቀለም ይሆናል፡፡

## 2.3.1. መሰረታዊ ቀለማትን መቀላቀል

ተማሪዎች መስራች ቀለማትን እርስ በእርሳቸው ሲቀላቅሉ ሌላ ቀለም ማለትም ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ማግኘት ሲቻል እንደገና አንደኛ (መስራች) ቀለማት ከሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ጋር ሲቀላቀሉ ሦስተኛ ደረጃ ከለማትን እንደሚፈጥሩ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ቀለማትን በመቀላቀል የምናገኘው ውጤት ለምንስለው ስዕል ትክክለኛውን መልክ አስመስለን መቀባት እንድንችል ይረዳናል ለዚህም ተግባር የሚረዱን ከአካባቢያችን በቀላሉ ከሚገኙ ቀሶች መቀቢየዎችን (ቡርሾችን) መስራት ከሚቻልባቸው መካከል ለሚሳሌ ከዶሮ ላባ ፤ ከእንስሳት ጸጉር(ጭራ) ፤ ከቃጫ ወዘተ… ከመሳሰሉት ቀጭን አንጨት ወይንም ጭራሮ ጫፍላይ በማሰር ለቀለም መቀቢያነት መጠቀም ይቻላል፡፡

መስራች ቀለማት እርስ በርሳቸው ወይንም አንዱ ከለላው ጋር ስቀላቀል ሁለተኛ ደረጃ ቀለማትን ይመሰርታሉ፡፡

- ሰማያዊ ቀለም ከቢጫ ቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት አረንጓዴ ቀለም ይሆናል፡፡
- -ቀይ ቀለምከቢጫ ቀለም ጋርሲቀላቀል የሚገኘው ውጤትብርትኩዋንማ ቀለም ይሆናል፡፡
- ሰማያዊ ቀለም ከቀይ ቀለምጋርሲቀላቀል
- የሚገኘው ውጤትወይንጠጅ ቀለም ይሆናል፡፡




*ስዕል 2.17 የመስራች ቀለማት ውጤት*

## መልመጃ 4

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ**

1. ቀይ ቀለም + ቢጫ ቀለም = ----------------?
2. ቀጥታ ህትመት ማለት ምንማለት ነው?
3. ሸካራነት ያላቸው ነገሮች ምነድናቸው?

## መልመጃ 4

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ**

1. ብረቱካናማ

2. ሽካራነት ያላቸው ቁሶችን ቀለም በመቀባት በነጭ ወረቀት ላይ ማተም


3. ቅጠሎች ፣ የዛፍ ቅርፊቶች ፣ የጣት አሻራ ወ.ዘ.ተ

## 2.3.2. ቀጥታ ህትመት

ቀጠታ ህትመት ማለት አንድ ተፈጠሮአዊ የሆነ ቁስ በአካሉ ላይ ለቀጥታ ህትመት አመቺ የሆነ ሽካራነትና ለስላሳነት እንዲሁም መስመሮች የሚገኙባችው ተፈጥሮአዊ አሊያም ሰው ሰራሽ ነገሮችን ምንም ተጨማሪ ዲዛይን ሳየታከልበት በቀጥታ ቀለም በመቀባት በንጹህ ወረቀት ላይ ወይንም በንጹህ ጨርቅ ላይ ማተም ማለት ነው።

ለምሳሌ፡- ከተፈጥሮ ሽካራነት ያላቸው የዛፍ ቅርፊቶች ፣ የተለያዩ የቅጠል ዓይነቶች ፣ የጣት አሻራ ወዘተ…

- ከሰው ሠራሽ የጫማ መርገጫ (የጫማ ሶል) ፣ የጠርሙስ ክዳኖች ፣ የጆኒያ ቁርጥራጭ ፣ ሽካራነት ያላቸው ጨርቃጨርቆች።



*ስዕል 2.18 ከአካባቢያችን ከሚገኙ ተፈጥሮአዊና ሰው ሠራሽ ቁሶችቀጥታ ህትመትን የሚያሳይ ስዕል*

***<u>መልመጃ ሁለት</u>***

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ**

1. ለቀጥታ ህትመት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ግለጹ
2. ቀጥታ ህትመት ከሌሎች የዕይታ ጥበባት አይነቶች በምን ይለያል፡፡
3. የህትመት ጠቀሜታን በዝርዝር ጻፉ፡፡

# 2.3. በተውኔት በተንቀሳቃሽ ምስሎችና ፎቶዎች ያሉ መልዕክቶች

*የክፍለ ጊዜ ብዛት =7*

### *መግቢያ*

*ተማሪዎች መልዕክት ማለት ምን ማለት ነው? መልእክት ስንል መናግር ፣ መስማት (ማዳመጥ) ፣ ማየት (መመልከት) ፣ መስጠት ፣ መቀበል የመሳሰሉት* የሰውልጆች በየእለቱ *ከሚያከናዉኗቸውና* ኑሮዋቸውን *ከሚመሩበት መንገድ* አንዱ በ*መሆኑ* ይገለገሉበታል፡፡ በ*መሆኑ*ም በ*ዕይታ* ጥበብውጥም *መልዕክቶች* በተለያዩ *መንገዶች* ከአንዱ ወደሌላው በ*መተላለፍ ታሪክን* ፣ ባህልን ፣ ትምህርትን ወዘተ… ከትውልድ ወደ ትውልድ በማስተላለፍ ለአንድ *ሀገር* እድገት ከፍተኛ ድርሻን ከ*መወጣት* ባሻገር በዚህ *ሙያ* ለሚተዳደሩ ዜጎች የገቢ ምንጭ ከ*መሆኑ*ም ባሻገር የእውቀት የሚሽ*ጋገ*ርበት *መንገድ* ነው፡፡

### ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ የሚጠበቅባቸው

- የ*መልዕከት ምንነትን መግለጽ*፡፡
- *መለዕክት የሚተላለፍባቸውን መንገዶች መ*ዘርዘር፡፡
- የ*መለዕክት* ጠቀሜ*ታን መናገር*፡፡
- ቀላል ፎቶ የማንሳት ዘዴን ይረዳሉ፡፡
- በፎቶ ውስጥ እንዴት *መልክቶችን ማስተላለፍ* እንዳለባቸው ይረዳሉ፡፡

***<u>የማንቂያ ጥያቄ</u>***

1. *ተማሪዎች* በቡድን *ሆናችሁ መልዕክቶች የሚተላለፉባቸውን መንገዶች* በ*ጋራ ተወያይታችሁ* በቡድን አቅርቡ
2. በአካባቢያቹ የ*ምታውቁትን መልዕክት ማስተላለፍያዎችን* በስ*ዕ*ል *ሠርታችሁ* አቅርቡ፡፡

## 2.3.1. በፎቶ ያሉ መልክቶች

ከዕይታ ጥበባት አንዱ የተንቀሳቃሽ ምስሎችና ፎቶዎች ተግባርና ክንውኖች የህብረተሰቡና ማህበረሰቡን የአኗኗር ዘይቤና ማህበራዊ ግንኙነቶችና እንዲሁም ወግ ባህል ታሪክና ሁለንተናዊ ገጽታዎችን ከሌሎች በአገራችን ላሉ ማህበረሰቦች ይህን መልካም ባህልና ታሪክ እንዲሁም በሚመዘግቡና ተቀርጸው በሚቀመጡ መዛግብቶችና የምስል ማከማቻዎችና ማስቀመጫዎች በእየታዊ ጥበብ አማካኝነት መልእክቶች በቀላሉ ከመተላለፋቸውም በሻገር መረጃንና ትምህርት ይሰጣሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ታሪካዊ ክንዋኔዎች

- ባህላዊ ክንዋኔዎች
- መንፈሳዊ ክንዋኔዎች

### *ታሪካዊ ክንዋኔዎች*

ኢትዮጵያዊያን ቅድመ አያቶቻችን የሀገራችን ዳር ድንበር ለማስክበር ከጠላት ጋር ያደረጉትን ተጋድሎ በተለያዩ የሥነ-ጠበብ መገለጫዎች አንዱ የዕይታ ጥበብ ሲሆን በዚህ ጥበብ የጀግኖችን ተጋድሎ ፣ ጊዜውን የሚያሳዩ የውጊያ መሳሪያዎች ጦር ፣ ጋሻ ፣ ጎራዴ እና የወቅቱ ዘመናዊ መሳሪዎች እንዲሁም የአገር ፍቅር የሚገለጽበት ሰንደቃላማ ባአጠቃላይ የተጋድሎ ቦታና አካባቢ በሚያሳዩ የሥነ-ጥበብና የእይታ ጥበብ እንዲሁም በፎቶና በተንቀሳቃሽ መስሎች መልዕክቶች መተላለፍ ይችላሉ፡፡



*ስዕል 2.19: የኢትዮጵያ ጀግኖች አገራቸውን ከጠላትወረራ የታደጉበትን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ*

**ባህላዊ ክንዋኔዎች፡-** በአገራችንና በአካባቢያችን የሚገኙ ማህበረሰቦች ዓመታዊና ወቅታዊ የተለያዩ ባህላዊ ክንዋኔዎችን በመተግበር ይታወቃሉ ፤ ባህላዊ ክንዋኔ ከምንላቸው

ለምሳሌ፡-

- ሠርግ
- ዘመን መለወጫ (እንቁጣጣሽ )
- ሀዘን (ለቅሶ)
- ልደት

ምረቃ (ምርቃት) የትምህርት ፤ የቤት እና በማህበረሰቡ የተሠሩ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን በሚያሳዩ የሥነ-ጥበብና የእይታ ጥበብ እንዲሁም በፎቶና በተንቀሳቃሽ መስሎች መልዕክቶች መተላለፍ ይችላሉ፡፡



*ስዕል 2.22 አገር በቀል ክንዋኔዎች ከሆኑት አንዱ ቡሄበሉ (ሆያሆየ) የሚገልጽ ስዕል።*



*ስዕል 2.23: የዘመን መለወጫ የአዲስ አመትመቀበያ (አበባ አየሽ ወይ) በህጻናት ሲዘመር*

➢ ሐይማኖታዊ ( መንፈሳዊ ) ክንዋኔዎች

በአገራችንና በአካባቢያችን በሚገኙ ማህበረሰቦች የተለያዩ ሐይማኖታዊና መንፈሳዊ ክንውኖች ይተገበራሉ በመሆኑም ማህበረሰቡ እንደ የአይነቱ የራሱን ሐይማኖታዊ እሴቱን በመጠበቅ ሐይማኖታዊ በዓላትን ያከብራል፡

ለምሳሌ፡-

- በክርስትና፡- የልደት፤ የጥምቀት፤ የስቅለት፤ የትንሳኤ (ፋሲካ) እና ወዘተ…
- በሙስሊሞች፡- የመውሊድ፤ አረፋ፤ ኢድአልፈጥር፤ ኢድ አልድሃ አና ወዘተ…

እነዚህ አገራዊና መህበረሰባዊ አንዲሁም አካባቢያዊ የሆኑ ሐይማኖታዊና መንፈሳዊ ትውፊቶችን በሚያሳዩ የሥነ-ጥበብና የእይታ ጥበብ እንዲሁም በፎቶና በተንቀሳቃሽ መስሎች መልዕክቶች መተላለፍ ይችላሉ፡፡



*ስዕል 2.24 ሐይማኖታዊ የጋብቻ ስነ-ስርዓት*



*ስዕል 2.27 ከሐይማኖታዊ ክንዋኔዎች አንዱ ከሆነው የጥምቀት በዓልን የሚገልጽ ስዕል*

**መልመጃ 6**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ

1. የፎቶዎችን ጥቅም ጥቀሱ
2. የተለያዩ ባህላዊ ክንውኖችን ዘርዝሩ

## 2.3.2. በተውኔት ያሉ መልክቶች

በዚህ ንዑስ ክ/ትምህርት ውስጥ ተማሪዎች ተውኔትን በመጠቀም እንዴት መልዕክቶችን ማስተላለፍ እነደሚቻል የሚያወቁበት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በምዕራፍ አንድ ስር የተማሩትን የትራጀዲ እና ኮሜዲ ደራማዎች ፅንሰ ሐሳብ በመነሳት በአካባቢያቸው እና በቤተሰቦቻቸው ዙሪ የሚመለከቱትን ወደ ደራማ በመቀየር እና ገፀ-ባህርያትን በመላበስ እየተወኑ ለክፍል ጓደኞቻቸው እና ለትምህረት ቤቱ ማህበረሰብ ያቀርባሉ፡፡

**ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- በተውኔት /ድራማን/ ተጠቅመው መልዕክትን በድራማ ያስተላልፉሉ፡፡
- በትውን ጥበባት እንዴት መልክት ማስተላለፍ እንደሚቻል ይረዳሉ፡፡

***<u>የማንቂያ ጥያቄ</u>***

1. ተውኔት ምንድነው?
2. እንዴት በተውኔት መልዕክት ማስተላለፍ ይቻላል?

ተውኔት የምንለው ቃል በምዕራፍ አንድ እንደተመለከትነው ድራማ የሚለውን ቃል ይወክላል ድራማ ፣ ድራማ ከመባሉ በፊት ጨዋታ እንደሚባል ሁሉ ተውኔትም ድራማን በመወከል ያገለግላል፡፡

ድራማ ወይም ተውኔት በመድረክ ላይ ተመልካቶችን በቀጥታ በማግኘት የሚከውን የትውናና ዕይታ ጥበብ ዘርፍ ውስጥ የሚገኝ ትውን ጥበብ ነው፡፡

በተውኔት መልዐክቶች ማስተላለፍ ሲባል ተውኔት የገሃዱን አለም ነፀብራቅ ለመድረክ በሚመጥን መልኩ የዕለት ከዕለት ኑሮን መጥኖ ወደ መድረክ ማቅረብ ሲለሆነ በተውኔት በርካታ ነጥቦችን መልዕክቶችን ማስተላለፍ ይቻላል፡፡ የተለያዩ ትምህርቶችን መልዕክቶችን ቀጥታ ከማስተላለፍ ይልቅ በድራማ (በተውኔት) እየተዝናኑ መልዕክቶችን እንዲያዳምጡ ማድረግ የተሻለ ነው፡፡

## በተውኔት እንዴት መልዕክት ማስተላለፍ ይቻላል

በምዕራፍ አንድ እንደተመለከትነው ድራማ ወይም ተውኔት በሁለት ይከፈላ አዝናኝ (አስቂኝ) እና አሳዛኝ ተብለው፡፡ በነዚህ ሁለቱ ክፍሎች ውስጥ የድራማ ታሪክ ወይም ድርሰት ይዘጋጃል፡፡ በተዘጋጀው ታሪክ ወይም ድርሰት ድንገት ፈጥረን ወይም ምጥን ተውኔትን ሊሆን ይችላል ወይም ባለአንድ ገቢር አልያ የሙሉ ጊዜ ተውኔት ሊሆን ይችላል ድርሰት ሲሆን ተዘጋጀው ጽሑፍ መሠረት ገፀ-ባህሪ በመከፋፈል አዘጋጅ ወይም ቡድኑን የሚመራ ሰው በመምረጥ የልምምድ ጊዜ በማውጣት መለማመድ ቃለ ተውኔቱን ማጥናት ስሜት ሰጥተው ድርጊቶች ጋር መተወን መለማመድ በደንብ ስሜቶች ድርጊቶቹ ስለሚሆኑ ያለ እንከን መተወን ሲቻል አስፈላጊ አልባሳት የገፀ-ቅብ (ሜካፕ) ፣ ቁሳቁስ ፣ የድምጽ ግበአት ፣ መብራት በመጠቀም አላስፈላጊ የሆኑትን በመተው በአዳራሽ ወይም ተመልካች በተሰበሰበበት መድረክ ማቅረብ ይቻላል፡፡

***መልመጃ 7***

1. ተማሪዎች በቡድን በመሆን አስቂኝ ምጥን ተውኔት መርጣችሁ አዘጋጅታችሁ አቅርቡ
2. ለቡድን በመሆን አሳዛኝ ምጥን ተውኔት አዘጋጅታችሁ አቅርቡ

## የተውኔት ዓይነቶች

ተውኔቶች በጊዜ ይከፋፈላሉ ዓይነቶችም በዛው ይለያሉ ማለትም ባለሙሉ ጊዜ ተውኔት ረጅም ጊዜና ሁለት እና ከዚያ በላይ ገቢር ያሉበት ባለአንድ ገቢር የምንለው ዳግም በአንድ ገብር የታጠረ መካከለኛ የጊዜ ቆይታ ያለው ነው፡፡

## ድንገቴ ፈጠራ

ድንገት ፈጠራ የተፃፈ ተውኔት ሳይኖር መጀመርያ መሀል መጨረሻ ኖሮት ማለትም ታሪክ ብቻ እና ገፀ-ባህርያት ተከፋፍለው የተወሰኑ ድርጊቶችን ተነጋግረው አኖረውት ያለ ቃለ ተውኔት በርዕስ ጉዳዩ ላይ ተዋንያኖች ከራሳቸው እየፈጠሩ ድርጊቶችን ጨምረው የሚተውኑት የተውኔት ዓይነት ነው፡፡

ተማሪዎች የሚከተለውን ታሪክ መሰረት አድርጋችሁ ቃላትን ከራሳችሁ ፈጥራችሁ በታሪኩ ቅደም ተከተል በድንገቴ ፈጠራ ተውኑ፡፡

## ታሪክ

አባት እናት ሁለት ወንድ እና ሴት ልጆች አንድ ላይ ይኖራሉ፡፡ ጥዋት ሲነሱ እናት ቁርስ ስታቀራርብ ልጆችን እናት አባታቸውን እንዲያስታጥቡ ስታዛቸው፡፡ አንች አስታጥቢ አንተ አስታጥብ እየተባባሉ ይጨቃጨቃሉ፡፡ እናት ከጓዳ ወታ ለምን እንደሚጣሉ ስትጠይቅ አንተ አንች አሳታጥቢ ተባብለው እንደሆነ ሲነግሯት እናት በጣም አዝና ሁለቱም ያደረጉት ትክል እንዳልሆነ ነግራቸው፡፡ ልጆች ሲታዘዙ እንደሚያድጉ ወደ ፊትም መልካም ነገር እንደሚገጥማቸው መሆን የሚፈልጉትን ታዘው ካደጉ መሆን እንደሚችሉ ስትነግራቸው እናታቸው ይቅርታ ጠየቁ፡፡ ተሽቀዳድመው እሷ በጆግ ውሃ እሱ ማስታጠቢያ ሳህኑን ይዞላት አባታቸውን ያስታጥባሉ አባታቸው ግንባራቸውን ስሞ ይመርቃቸዋል እደጉ ተመንደጉ ያሰባችሁት ሁሉ ይሙላላችሁ ለሀገራችሁ ኢትዮጵያ ዘብ የምትቆሙ እድገቷን የምታፋጥኑ ከጥላቶቿ የምትጠብቁ ሆናችሁ እደጉ፡፡ ወንዱ ልጅ አባዬ ኢትዮጵያ ሀገራችን ጠላቶቿ እነማን ናቸው? እናት ልጆቼ ከውጭ ሆነው ስለሀገራችን መጥፎ የሚናገሩ የሚያደርጉ ፈረንጆች አሉ ነገር ግን ፈረንጆች ሁሉም ጠላት አይደሉም ለኢትዮጵያ ሀገራችን መልካም የሚያደርጉ ፈረንጆችም አሉ፡፡ ሴት ልጅ አድጋ የሀገራችንን ጠላቶች ማጥፋት ነው ምፈልገው፡፡ አባት ልጆች

የሀገራችን ጠላቶች ማጥፋት የምንችለው ባለንበት በርትተን ጠንክረን ጎብዘን ከሰራን ድህነታችንን ካጠፋን ከጎበዝን ጠላቶቿ ሁሉ በራሳቸው ጊዜ ይጠፋሉ። እናት ጠንክራችሁ ጎብዛችሁ እየተማራችሁ እየሰራችሁ እርስ በእርሳችሁ ከተዋደዳችሁ ጠላት ድራሽ አባታቸው ነው ሚጠፋው። አባት በሉ እኔ ስራ ልግባ እናንተን ት/ቤት ልሸኛችሁና አንችም ተነሽ እንሂድ (ተነስተው ደብተራቸውን ይዘው አብረው ይወጣሉ)።

## የትምህርቱ ማጠቃለያ

ድምፆች ባላቸው ባህሪያት መደበኛ (ሙዚቃዊ) እና መደበኛ ያልሆኑ (ኢ-ሙዚቃዊ) ብለን በሁለት እንከፍላቸዋለን፡፡

መደበኛ (ሙዚቃዊ) ድምፆች የምንላቸው ውስን በሆነ የድምፅ እርግብግብታ የሚፈጠሩ እና ለጆሮ የማይረብሹ ወይም የሚመቹ ሙዚቃዊ ድምፆች ሲሆኑ እነዚህንም ድምፆች በአካባቢያችንም ሆነ በአለማችን ለሙዚቃ ስራ ምንጠቀምባቸው ናቸው፡፡

መሠራች ቀለማት እርስበራሳቸው ወይም አንዱ ከሌላውጋር ሲቀላቀል ሁለተኛደረጃ ቀለማትን ይመሰርታሉ፡፡ ቀጥታ ህትመት ማለት አንድ ተፈጠሮአዊ የሆነ ቁስ በአካሉላይ ለቀጠታ ህትመት አመቺ የሆነ የሸካራነትና ልስላሴነት እንዲሁም መስመሮች የሚገኙባቸው ተፈጥሮአዊ አሊጣም ሰውሰራሽ ነገሮችን ምንም ተጨማሪ ዲዛይን ሰይታከልበት ቀለም በመቀባት በቀጥታ በወረቀት ወይም በጨርቅላይ ማተም ነው

ለምሳሌ ያህል በገበያ አካባቢ የምንሰማቸው ሁካታዎች ፣ ከመጠን በላይ ጮክ ብሎ የሚሰማ ሙዚቃ ፣ የትራፊክ መጨናነቅ በሚበዛበት አካባቢ የሚሰሙ የመኪና ጥሩንባወች ወ.ዘ.ተ. ሲሆኑ እነዚህ አይነት ድምፆች አዕምሮን የሚረብሹ እና ጤናንም የሚጎዱ ድምፆች ናቸው፡፡


በአለማችን ውስጥ በርካታ ማህበረሰቦች ይገኛሉ እነዚህ ማህበረሰቦችም የራሳቸው የሆነ ወግ ፣ ባህላዊ ውዝዋዜ/ዳንስ/ ፣ ሙዚቃ ወ.ዘ.ተ አሏቸው፡፡ በዚህም አስተሳሰባቸውን ፣ ፍላጎታቸውን ፣ አኗኗራቸውን ፣ ሀዘናቸውን ፣ ደስታቸውን ወ.ዘ.ተ. ለመግለፅ ከሚጠቀሙባቸው የጥበብ መንገዶች ውስጥ አንደኛው የጥበብ መንገድ ሙዚቃ ነው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**ትዕዛዝ 1፡ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ስጡ**

1) ድምፅ እንዴት ይፈጠራል?
2) ስንት አይነት ድምፆች አሉ?
3) ሙዚቃዊ/መደበኛ/ ድምጽ የምንላቸው ምን አይነት ድምፆችን ነው?
4) ኢ-ሙዚቃዊ/ኢ-መደበኛ/ ድምጽ የምንላቸው ምን አይነት ድምፆችን ነው?
5) ድምፅ ማለት ምን ማለት ነው?
6) ሃለካ የምንለው የሙዚቃ መሳሪያ ከምን ይሰራል?
7) በቀድሞ ጊዜ ነገስታት አዋጅ ለማወጅ እና በጦርነት ወቅት መልዕክት ለማስተላለፍ ይጠቀሙበት የነበር የምት የሙዚቃ መሳሪያ ምን ይባላል?
8) ከከበሮ ጋር ተመሳሳይነት ያለው የምት የሙዚቃ መሳሪያ ማን ይባላል?

**ትዕዛዝ 2፡-ከዚህ በታች የተቀመጡትን የኖታ እና የእረፍት ምልክቶች የምት የሙዚቃ መሳሪያን በመጠቀም ለማንበብ ሞክሩ**



**ትዕዛዝ 3፦ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልሱ**

1) ቀላል የሆኑ ባለሁለት አውታረመጠን ዝርግ ቅርጾች ማለት እይታዊ ጥበብ ውስጥ የሚገለጹት በውጫዊ መስመር ነው፡፡
2) ባለሁለት አውታረመጠን ዝርግ ቅርጾች በተፈጥሮአዊ እና በሰው ሠራሽ ቁሾች በነጠላ መስመር በመንደፍ የሚገለጽበት መንገድነው፡፡
3) ባለ ሦስት አውታረመጠን ቅርጽ ወይም ቁስ ማለት የሚዳሰስ፤የሚጨበጥ፤ እንዲሁም ርዝመት፤ ቁመት፤ጥልቀት ያለው አካል ማለት ነው፡፡
4) መስራች ቀለማት እርስበራሳቸው ወይም አንዱ ከሌላው ጋር ሲቀለቀል ሦስተኛ ደረጃ ቀለማትን ይመሰርታሉ፡፡
5) ሰማዊ ቀለም ከቢጫቀለም ጋር ሲቀላቀል የሚገኘው ውጤት ብርትኳንማ ቀለም ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ 3

## 1.ባህላዊ ገለፃዎች

*የክፍለ ጊዜ ብዛት = 20*

### መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ በቀደሙት የጥበብ አባቶቻችን የተሰሩ የእይታና ትውን ጥበባትን የምን ቃኝበት ነው፡፡ የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ በኑሮው ውስጥ የሚገጥሙትን የተለያዩ የደስታ ፣ የሐዘን ፣ የፍቅር ወ.ዘ.ተ. አጠቃላይ የኑሮ ውጣ ውረዶችን በተለያዩ የእይታ እና የትውን ጥበባት በመግለፅ አኗኗራቸውን ሲያንፀባርቅ ይታያል፡፡

የሰው ልጆች እንደየ አካባቢያቸው የአየር ንብረት ሁኔታ እና አኗኗር የተለያየ አይነት አለባበስ ፣ የቤት አሰራር ፣ ባህል ፣ ውዝዋዜ ፣ ሙዚቃ ወ.ዘ.ተ. አሏቸው፡፡ ይህም ሲባል ሰዎች ስሜታቸውን በሙዚቃ እና መሰል የጥበብ ስራዎች ከመግለፅ ባለፈ በአለባበሳቸውም ስሜታቸውን ማንፀባረቅ ይችላሉ፡፡

በዚህ ምዕራፍም ቀደምት አባቶቻችን የትውን እና እይታ ጥበባትን ተጠቅመው የሰሯቸውን ስራዎች ከማየት ባለፈ የአለባበስ እና የቤት አሰራራቸውን ለመቃኘት እንሞክራለን፡፡

### ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

- በማህበረሰባቸው አካባቢ የሚዜሙ ቀደምት የባህል ሙዚቃዎችን ምን ይመስሉ እንደነበር ይቃኛሉ ይጫወታሉ፡፡
- በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ የሚታዩትን የባህል አለባበስ ይቃኛሉ፡፡
- በቀደምት የጥበብ አባቶች የተሰሩ የትውን እና እይታ ጥበባት ስራዎችን ከአሁኑ ዘመን ጋር ያወዳድራሉ፡፡

- በአካባቢያቸው የሚታወቁ ባህላዊ ዜማዎችን ፣ ዘፋኞችን እና ስራዎቻቸውን ይቃኛሉ
- በአካባቢያቸው የሚታወቁ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን እና ሙዚቃዎችን የቀደሙትን ከአሁኑ ዘመን ጋራ በማወዳደር ይለያሉ፡፡
- የተለያዩ ተፈጥሮ መስህቦችን እና ባህላዊ ቦታዎችን በመጎብኘት የፅሑፍ ዘገባ ያቀርባሉ፡፡

## 3.1. ባህላዊ ብዝሀነት ባለፈው እና በአሁኑ ጊዜ በእይታና የትውን ጥበባት ሲቃኝ

*የክፍለ ጊዜ ብዛት = 20*

***መግቢያ***

ባህል ማለት በአገራችን አካባቢችን በሚገኙ ማህበረሰቦችና ህዝቦች የሚተገበርና በየጊዜው የሚከወን ተግባርነው፡፡ በመሆኑም በማህበረሰቡ ውስጥ እንደ የማህበረሰቡ አኗኗርና ማህበረሰቡን የሚገልጹ የሀዘን ፣ የሠርግ እና የተለያዩ ዓለማዊና ሐይማኖታዊ በዓላት በአካባቢያችንና በአገራችን እንዲሁም በመላው ኢትዮጵያ ባህላዊ ብዝሀነትን ጠብቆ በማህበረሰቡ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ባህላዊ ብዙሀነት ባለፈውና በአሁኑ ጊዜ በእይታ ጥበብ ሲቃኝ ማህበረሰቡ በዘመኑና ጊዜው ከተማረና ከሰለጠነ አኗኗሩ ስለሚቀየር ባህሉም ከባለፈው የአሁኑ ጊዜ ዘመናዊነትን የተላበሰ በመሆኑ ባለፈው ጊዜ ይተገበር የነበረው የቤት አሠራር ፣ አለባበስ ፣ አመጋገብ ፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች ባጠቃላይ ከዘመኑ ስልጣኔ አኳያ ስለሚቀየር በእይታ ጥበብ አኳያ ሲቃኝ የባለፈውና የአሁኑ ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ በመሆኑም ልዩነቶችም በተለያዩ የስነ-ጥበብና የእይታ ጥበብ አማካኝነት ተቀርጸው በመቀመጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንድሻገሩ መደረግ አለባቸው፡፡

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ የሚጠቁ ውጤቶች

- የባህላዊ ገለጻ ምንነትን መናግር
- ባህላዊ ገለጻና የእይታ ጥበብን ማነጻጸር
- ባህላዊ ገለጻዎች ከታሪክ ዐውድ ጋር ያላቸውን ግኑኝነት መረዳት
- ባህላዊና ታርካዊ የእይታ ጥበቦችን መጠበቅ ና መንከባከብ

*ማንቂያ (መሪ ተግባራት)*

1. ባህላዊ ገለጻ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ተማሪዎች ባህል ስንል  ምን ማለት ይመስላችኋል?

ታሪክና ባህል በእይታ ጥበብ እንዴት ይገለጻሉ የሚሉትን ጥያቀዎች ለተማሪዎች በቡድን ተወያይተው በቡድናቸው አለቃ አማካይንት እንዲያቀርቡ ማድርግ፡፡

ባህል ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ የሆነው የእይታ ጥበብ ነው፡፡ በዚህ የእይታ ጥበብ በሀገራችን የሚገኙ ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ እሴቶችን መዝግቦና ቀርጾ የስቀራል፡፡ ካለፈው ትውልድ የተላለፉትን የእይታ ጥበባትና የተለያዩ የኪነ-ጥበብና የሥነ-ጥበብ ውጤቶች ከአሁኑ እና ዘመኑ ከደረሰበት ስልጣኔ ደረጃ አንጻር ጎን ለጎን በማስኬድና በማስቀመጥ የማህበረሰቡን የአኗኗር ፣ የአለባበስ ፣ ሀዘንና ደስታ እንዲሁም የቤት አሰራራቸውን ጨምሮ በተለያዩ የእይታ ጥበባትና የኪነ-ጥበብና የሥነ-ጥበብ አመዘጋገብ ስልቶች ቀርጾ በማስቀመጥ እንደ ቅርስና እንደ ታሪክ ዐውድ ከዘመን ዘመን ይሻገራል፡፡ ተማሪዎችም ባህላዊ እሴትንና ታርክን መንከባከብና መጠበቅ እንዲችሉ መማርና ማወቅ አለባቸው፡፡

## *የተግባር መልመጃ 1*

1. ተማሪዎች አራት ቡድን በመመስረት እና የባህል አልባሳትን በመልበስ ቀደም ያሉ አባቶች በተለያዩ ክብረ በአላት ላይ ይጫወቷቸው የነበሩ የተለያዩ ባህላዊ ዜማዎችን ለክፍል ጉደኞቻችሁ አቅርቡላቸው፡፡



*ስዕል 3.3 ባህላዊ ገለጻዎችን የሚያሳዩ ስዕሎች*

### የትምህረት መርጃ መሳሪያ

- ምቹ የመለማመጃ ክፍል
- ስዕሎች
- ድምፅ እና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻዎች
- ፎቶዎች
- ሙዚቃ ማጫወቻ
- እርሳስ ባለቀለም
- የባህል ሙዚቃዎች የተቀረፁበት ሸክላ
- በአካባቢያቸ የሚገኙ የስዕላ ግብአቶች

*የአፅምሮ ማንቂያ*

1. በባህላዊ አለባበስ ባህላዊ ውዝዋዜዎችን እንዲያቀርቡ ማደረግ
2. ስለባህላዊ አለባበስ ውዝዋዜ እና ሙዚቃ ቀድሞ የነበራቸውን ግንዛቤ መጠየቅ

## ጠቃሚ መረጃ

ባህል ከሚገለጽባቸው መንገዶች አንዱ የሆነው የእይታ ጥበብ ነው ፤ በዚህ የእይታ ጥበብ በሀገራችን የሚገኙ ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ እሴቶችን መዝግቦና ቀርጾ በማስቀረት (በማስቀመጥ) ካለፈው ትውልድ የተላለፉትን የእይታ ጥበባትና የተለያዩ የኪነ-ጥበብና የሥነ-ጥበብ ውጤቶች ከአሁኑ እና ዘመኑ ከደረሰበት ስልጣኔ ደረጃ አንጻር ጎን ለጎን በማስኬድና በማስቀመጥ የማህበረሰቡን የአኗኗር ፣ የአለባበስ ፣ ሀዘንና ደስታ እንዲሁም የቤት አሰራራቸውን ጨምሮ በተለያዩ የእይታ ጥበባትና የኪነ-ጥበብና የሥነ-ጥበብ አመዘጋገብ ስልቶች ቀርጾ በማስቀመጥ እንደቅርስና እንደ ታሪክ ዐውድ ከዘመን ዘመን እንዲሻገርና ተማሪዎችም ባህላዊ እሴትንና ታርክን መንከባከብና መጠበቅ እንዲችሉ መማርና ማወቅ አለባቸው፡፡

### ጠቃሚ መረጃ

- ልጆቹ ባህላዊ ፌስቲቫሎች ወዳሉበት ቦታ በጉብኝት መለኩ መወሰድ እና ከጉብኝቱ በኋላ ያዩትን እና የሰሙትን በፅኑፍ እና በዘገባ እነዲያቀረቡ ማደረግ

## የመማር ማስተማር ክንዋኔ

- ተማሪዎችን ባህላዊ ሙዚቃዎች የምንላቸው ምን አይነት ሙዚቃዎች እነደሆኑ መተየቅ
- በአካባቢው ካሉ የባህል ዘፋኞች በመጋበዝ እነዲወያዩ ማድረግ

- ተማሪዎችን ስለ ባህል ዘፋኞች እና ተወዛዋዥች ቡድን መስርተው እንዲወያዩ ማድረግ
- በቡድን የተወያዩትን እና የተረዱትን እንዲገለፁ ማድረግ እና በገለፃ ወቅትም ማበረታታት
- ስለቀደሙ የባህል ዘፋኞች እና ተወዛዋዥች ሰፋ ያለ ገለፃ ማድረግ
- የተወሰኑ አካባቢ ውዝዋዜዎችን በመምረጥ በወስጣቸው የሚንፀባረቁ ነገሮችን ተማሪዎቹ እመዲመራመሩ ማደረግ

### 1.1.1. ባህል ቅርስ እና የተፈጥሮ መስህቦች

ኢትዮጵያ የበርካታ ባህል እና የተፈጥሮ መስህቦች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ እነዚህንም የባህል እና የተፈጥሮ መስህቦች በተለያዩ የሃገራችን ቦታዎች እናገኛቸዋለን፡፡


ኢትዮጵያ በዓለማችን እጅግ ጥንታዊ የስልጣኔ ታሪክ ያላት ክርስትናን እና እስልምናን ፣ የዋቂፈና እምነትን ጨምሮ የበርካታ ሀይማኖት ተከታዮች በፍቅር እና በአንድነት የሚኖሩባት ድንቅ አገር ናት፡፡ በቅድመ ሰው ዘር ጥናትም የመጀመሪያ የሰው ዘር መኖሪያ /መገኛ/ ፣ ቡናን ለዓለም ያስተዋወቀች የበርካታ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ባለቤት የሆነች አገር ናት፡፡ አገራችን በተለየ ሁኔታ የቋንቋ እና የባህል ብዝሃነት የሚታይባት ባህላዊ እና ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤዎች በኪነ-ጥበብ ፣ በስነ-ጥበብ እና በእደ-ጥበብ አዋዝታ ማራኪ ዕይታዎችን የፈጠረች አስደናቂ እና አስደማሚ አገር ናት፡፡ ለዚህም የሥልጣኔ ፣ የባህል እና የታሪክ ባለቤት ለመሆኗም ከአስራ ሁለት በላይ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች በዓለም አቀፍ መድረክ በዮኔስኮ በማስመዝገብ ታላቅነቱን ያስመሰከረች ሃገር ናት፡፡ ይህም የሰው ልጆች ሁሉ ቅርስ የሆኑ ሃብቶችን ያቀፈች የዓለማችን ድንቅ አገር ያደርጋታል፡፡

ኢትዮጵያ ካሏት እጅግ ብዙ የባህል ሀብቶቿ ውስጥ በማይዳሰሱ ቅርሶች ዘርፍ ሙዚቃው እና ውዝዋዜውን እናገኛለን፡፡ ሙዚቃ እና ውዝዋዜ እረገድ

ሀገራችን ያላት አቅም ከፍተኛ እና ቀደምት ከሚባሉት የሚመደብ ነው፡፡ የምዕራቡ አለም ዘመን የማይሽራቸው /ክላሲካል/ ብሎ የሚመፃደቅባቸውን የእነ ሞዛርት እና ቤትሆቨን ስራዎች በ14ኛው ክ/ዘመን ከመውጣታቸው በፊት ኢተዮጵያዊው የሙዚቃ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ጥልቅ እና መንፈስን የሚያድሱ እስከዛሬ ድረስ ዘመናትን የተሻገሩ ማህሌታዊ ዜማዎችን የደረሰው በ6ኛው መቶ ክ/ዘመን ነበር፡፡ አለም የሙዚቃ ድምፆችን በምልክቶች እየወከለ ዶ ፣ሬ ሚ….. እያለ እና የኖታ እና የእረፍት ምልክቶችን ቀርፆ ከመፃፉ ከብዙ መቶ አመታት በፊት ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ጭረት፣ ድፋት ርክርክ፣ ውርድ፣ ይዘት፣ ድፋት፣ቅናት ወ.ዘ.ተ ብሎ የዜማ ምልክቶችን በመስራት /በመቅረፅ/ በመቋሚያ ዜማን መርቷል፡፡ ለዚህም ነው አገራችን የቀደምት ስልጣኔ ፈር ቀዳጅ የባህል እና የታሪክ ባለቤት የቋንቋ እና የባህል ብዝሃነት የሚታይባት ባህላዊ እና ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤዎች በኪነ-ጥበብ፣ በስነ-ጥበብ እና በእደ-ጥበብ አዋዝታ በማቅረብ ማራኪ ዕይታዎችን የፈጠረች አስደናቂ እና አስደማሚ አገር ናት የምንለው፡፡ ስለ ሃገራችን ኢትዮጵያ ይህንን ያህል ካልን በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን /በአካባቢያችን/ ያሉ ባህላዊ የውዝዋዜ እና የሙዚቃ ስራዎችን እንመልከት፡፡



*ስዕል 3.4 ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ለንጉስ ገ/መስቀል በቤተ-መንግስታቸው ዜማ ሲጫዎትላቸው የሚያሳይ ምስል*




*ስዕል 3.5 የቅዱስ ያሬድ የኖታ ምልክቶች*

## ከዚህ ክፍለ ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች

- በአካባቢያቸው የሚታዎቁ ባህላዊ ዜማዎችን እና ውዝዋዜዎችን ይተዋወቃሉ
- በአካባቢያቸው ያሉ የተፈጥሮ መስህቦችን እንዲያውቁ ይደረጋል
- በአካባቢያቸው ያሉ የተፈጥሮ መስህቦችን በምስል በድምፅ እና በአካል እንዲለዩ ማድረግ

## አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎች

- ገለፃ
- ውይይት
- ተግባራዊ ልምምድ
- ጥያቄ እና መልስ

- በዝማሬ የማስተማር ስልት
- አስመስሎ መስራት (መተወን)

## የትምህረት መርጃ መሳሪያ

- ስዕሎች
- ፎቶዎች
- ሙዚቃ ማጫወቻ
- ምስል ማጫወቻዎች
- የባህል ሙዚቃዎች የተቀረፁበት ሸክላ

**የአዕምሮ ማንቂያ፡-**

- ከአሁን በፊት ተማሪዎች ስለጎበኟቸው ቦታወች መጠየቅ

**አጠቃላይ የክትትልና ግምገማ ዘዴዎች፡-**

- የጽሑፍና የቃል ጥያቄ ፣
- በተግባር የሚከናወኑ ሥራዎች ምልከታ

*<u>የተግባር መልመጃ 1</u>*

1. ተማሪዎችን በአራት ቡድን በመክፈል እና የባህል አልባሳትን እንዲለበሱ በማድረግ ቀደም ያሉ አባቶች በተለያዩ ክብረ በአላት ላይ ይጫወቷቸው የነበሩ የተለያዩ ባህላዊ ዜማዎችን ለክፍል ጉደኞቻቸው እንዲቀርቡ ማድረግ፡፡

**አተገባበር**

- ተማሪዎችን በአራት ቡድን መክፈል
- ተለያዩ የባህል አልባሳትን እንዲለበሱ ማድረግ
- በተለያዩ ክብረ በአላት ላይ የሚዜሙ እንደ ቡሄበሉ፣ሆያሆየ፣ የሰርግ ዜማዎችን፣ በክብረ በዓላት የሚዜሙ የተለያዩ ዜማዎችን ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉ ሙዚቃዎችን እንዲጫወቱ እና እነዲወዛወዙ ማድረግ፡፡

### 3.1.2. ታሪካዊ ቦታዎች እና የተፈጥሮ መስህቦች

ታሪካዊ ቦታዎች የምንላቸው በቀድሞ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ጥንት አባቶቻችን የሰሯቸው ስራዎች ሲሆኑ እነዚህ ጥንታዊ እና ታሪካዊ ቦታዎችን መጎብኘት የቀድሞውን ዘመን የሰዎችን አኗኗር እንድናውቅ እና እንድንረዳ ከማደረጉም በላይ የዛሬ ማንነታችንን እንድንረዳ ያደረጉናል፡፡ በሌላ በኩል የተፈጥሮ መስህቦች የምንላቸውም አምላክ /ፈጣሪ/ በኪነ ጥበቡ አስውቦ እና አሳምሮ የሰራቸው እና ያስቀመጣቸው ለመንፈስ እርካታ ለአዕምሮ ደስታን የሚያጎናፅፉ ውብ  የተፈጥሮ መስህቦች ናቸው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም የሰው ልጅ እነዚህን ታሪካዊ ቦታዎች እና የተፈጥሮ መስህቦች ከመጎብኘት እና ከማወቅ ባለፈ ሊጠብቃቸው እና ተንከባክቦ ለመጭው ትውልድ ሊያስረክባቸው ይገባል፡፡

**ከዚህ ክ/ትምህርት በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቁ ውጤቶች፡-**

- በሚኖሩበት አካባቢ ያሉ የተፈጥሮ መስህቦችን እና ታሪካዊ ቦታዎችን ይጎበኛሉ ይተዋወቃሉ፡፡
- በሚኖሩበት አካባቢ ያሉ የተፈጥሮ መስህቦችን እና ታሪካዊ ቦታዎችን እንዴት መጠበቅ እና መንከባከብ እንዳለባቸው ግንዛቤ ይይዛሉ፡፡
- የተፈጥሮ መስህቦችን እና ታሪካዊ ቦታዎችን በእይታና ትውን ጥበባት እንዴት ለሌሎች ማስተዋወቅ እንዳለባቸው መጠነኛ ግንዛቤ ይጨብጣሉ፡፡

## ሀ. ታሪካዊ ቦታዎች

***<u>የማንቂያ ጥያቄ፡-</u>***

1. ከአሁን በፊት ተማሪዎች የጎበኟቸውን ታሪካዊ ቦታዎች መጠየቅ፡፡ የጎበኟቸው ቦታዎች የት እና መቼ እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ፡፡ ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችህ ንገሩ፡፡
2. በመኖሪያ አካባቢያቸው ምን አይነት ታሪካዊ ቦታዎች እንዳሉ መጠየቅ?

3. በሚኖሩበት አካባቢ ለሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎች እንክብካቤ ማድረግ አለማድረጋቸውን መጠየቅ፡፡ ከሆነ እንዴት? እና በምን መንገድ?

ኢትዮጵያ የበርካታ ታሪኮች ባለቤት ናት፡፡ ቀደምት አባቶቻችን ከሰሯቸው ስራዎች መካከል የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ፣ የአክሱም ሃውለቶች የሐረር ግንብ ፣ የነጃሽ መስኪድ ፣ የሶፍ ዑመር ዋሻ ወ.ዘ.ተ. ከብዙ ጥቂቶቹ ሲሆኑ የአድዋ ድል የገኘበት የአደዋ ተራሮችም ከታሪካዊ ቦታዎች ውስጥ በዋነኝነት የሚጠቀስ ነው፡፡

ቀደም ባለው ጊዜ በዲራይታ "ሆርማ ቃሎ" ተብሎ ይጠራ የነበረው እና ሞስየ ፣ ማሾሌ ፣ ኩስሜ ፣ ደራሼ የተባሉ ጎሳዎች የሚገኙበት በቀድሞው የጋሞ ጎፋ ዞን ውስጥ የሚገኘው የጋረዱላ ተራራ ደግሞ በደቡብ ኢትዮጵያ ውስጥ ከምናገኛቸው ቀደምት እና ታሪክ ጠገብ ቦታዎች አንዱ ነው ፡፡

ጋርዱላዎች እንደ ቀደምቶቹ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ማዕከላዊ መንግስት ወደ አካባቢው ከመዝለቁ በፊት በራሳቸው የስልጣኔ ጎዳና ሐይማኖት ፣ ባህል ወግ እና የኢኮኖሚ ስርአት መስርተው ይኖሩ እንደነበር ታሪክ ይናገራል

በ1883 ዓ.ም ከአፄ ምኒሊክ የጦር አዝማቾች መካከል በራስ ሉዑል ሰገድ ይመራ የነበረው ጦር ሲዳሞን ካስገበረ በኋላ በደጃች ገነሜ አዝማችነት ወደ ጋርዱላ በመምጣት አካባቢውን የኢተዮጵያ ንጉሳዊ መንግስት አካል እንዳደረጉት ታሪክ ይናገራል፡፡ ራስ ልዑል ሰገድ አካባቢውን ከኢትዮጵያ ጋር ከቀላቀሉት በኋላ በቀጣይ ለሚያደርጉት መስፋፋት እንደ ዘመቻ መምሪያ /የዕዝ ማዕከል/ አድርገው የተጠቀሙት ታሪካዊውን የጋረዱላ ተራራ ነበር፡፡ ዛሬ ጋረዱላ የሚለውን መጠሪያም የተገኘው ደራሼዎች "ሆርማ ቃሎ" የሚሉትን የሸዋ ኦሮሞ ዘማች ወታደሮች በኦሮምኛ "ካራ ዱላ" ወይም የዘመቻ መንገድ እያሉ በመጥራታቸው ነው፡፡

## ለ. ተፈጥሯዊ መስህቦች

***የማንቂያ ጥያቄ፡-***

1. ተፈጥሯዊ መስህቦች የምንላቸው ምንድን ናቸው?
2. የተፈጥሮ መስህብ ያሉባቸውን ቦታዎችን ጎብኝታችሁ ታውቃላችሁ? ከሆነስ የት? ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችህ ንገሩ?
3. በምትኖሩበት አካባቢ ምን አይነት የተፈጥሮ መስህቦች ይገኛሉ?
4. በምትኖሩበት አካባቢ ለሚገኙ የተፈጥሮ መስህብ ለሚገኙባቸው ቦታዎች እንክብካቤ አድርጋችሁላቸው ታወቃላችሁ? ከሆነ እንዴት? በምን መንገድ?

ተፈጥሯዊ መስህቦች የምንላቸው አምላክ /ፈጣሪ/ በኪነ-ጥበቡ አስውቦ እና አሳምሮ የሰራቸው እና ያስቀመጣቸው ለመንፈስ እርካታ ለአዕምሮ ደስታን የሚያጎናፅፉ ውብ የተፈጥሮ መስህቦች ናቸው፡፡ በመሆኑም ማንኛውም የሰው ልጅ እነዚህን ታሪካዊ ቦታዎች እና የተፈጥሮ መስህቦች ከመጎብኘት እና ከማወቅ ባለፈ ሊጠብቃቸው እና ተንከባክቦ ለመጭው ትውልድ ሊያስረክባቸው ይገባል፡፡ የተፈጥሮ መስህብ ያላቸውን ቦታዎች መጠበቅ እና መንከባከብ በተፈጥሮ መስህቦች ልናገኘው ከምንችለው የመንፈስ እርካታ እና የአዕምሮ ደስታ ባለፈ ንፁህ ፅዱ እና የተዋበ የመኖሪያ አካባቢ እንዲኖረን እና ከተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ድረቅ ፣ ከፍተኛ ሙቀት ጎርፍ የመሬት መሸርሸር ወ.ዘ.ተ ለመጠበቅ ያስችለናል፡፡

### አጠቃላይ የመማር ማስተማር ሥነ-ዘዴዎች

- ከት/ት ቤቱ አስተዳደር እና ሀላፊዎች ጋር በመነጋገር በገና የእረፍት ጊዜያችው ተማሪዎችን የተለያዩ የተፈጥሮ መስህቦች እና ታሪካዊ ቦታዎች ወዳሉባቸው ቦታዎች በመሄድ እንዲጎበኙ ማድረግ፡፡
- በጉበኝታቸው ወቅት ስለቦታዎቹ ገለፃ ማድረግ፡፡
- በገለፃ እና በጉብኝት ወቅት ተማሪዎች ማስተዋሻ እንዲይዙ ማድረግ፡፡

- ስለጎበኟቸው ቦታዎች እንዲወያዩ የውይይት ጊዜ እና ቦታዎች ማመቻቸት፡፡
- የተፈጥሮ መስህቦች እና ታሪካዊ ቦታዎች የመንከባከብተግባራዊ ልምምድ እንዲያደርጉ ማገዝ፡፡
- ስለጎበኟቸው ቦታዎች ጥያቄ እና መልስ በማዘጋጀት ተማሪዎችን ማሳተፍ፡፡
- ስለጎበኟቸው የተፈጥሮ መስህቦች እና ታሪካዊ ቦታዎች ዘገባ እነዲያቀርቡ ማድረግ፡፡


ከዚህ በታች በጋሞ ዙሪያ የሚገኙ ተፈጥሯዊ ቦታዎች ስም እና ምስል ተቀምጧል፡፡



*ስዕል 3.7 የነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ እና የአባያ ሐይቅ /አርባ ምንጭ/*



*ስዕል 3.8 ከፊት ለፊት የነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ መሃል የእግዜር ድልድይ በስተ ግራ የአባያ ሓይቅ በስተ ቀኝ የጫሞ ሓይቅ*



ስዕል 3.9 ኮንሶ የሚገኘው ኒው ወርክ የተባለው ተፈጥሯዊ ቦታ



*ስዕል 3.10 ኮንሶ የሚገኘው ኒው ወርክ የተባለው ተፈጥሯዊ ቦታ*

***<u>የመልመጃ -2 መልስ</u>***

1) በቀደምት አባቶቻችን የተሰሩ የኪነ-ጥበብ ስራዎች፣ተጋድሎዎች ወ.ዘ.ተ ቦታዎች፡፡
2) በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት በጋሞ ዞን ደራሼ ወረዳ፡፡
3) ስለ አለፉት አባቶቻችን የጥበብ ስራ እና ተጋድሎ በማወቅ ታሪክን ከመጭው ዘመን ጋር በማቆራኘት የተሸለ ነገር ለመፍጠር፡፡
4) ለመጭ ትውልድ ታሪክን ለማስረከብ፣ በቱሪዝም የሀገር ገቢን ለማሳደግ ወ.ዘ.ተ፡፡

***የመልመጃ 3 መልስ***

1) ተፈጥሯዊ መስህቦች የምንላቸው የምንላቸው አምላክ/ ፈጣሪ/ በኪነ ጥበቡ አስውቦ እና አሳምሮ የሰራቸው እና ያስቀመጣቸው ለመንፈስ አርካታ ለአዕምሮ ደስታን የሚያጎናፅፉ ውብ የተፈጥሮ መስህቦች ናቸው፡፡
2) በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት በጋሞ ዞን አርባ ምንጭ ከተማ ዙሪያ፡፡
3) ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግስት
4) ለመንፈስ አርካታ ለአዕምሮ ደስታን የሚያጎናፅፉ ውብ የተፈጥሮ መስህቦች በመሆናቸው፡፡
5) አካባቢን ከተለያዩ የተፈጥሮ አዳጋዎች ለመጠበቅ የሚያስችል በመሆኑ፡፡

### 3.1.1. በጉብኝት ወቅት እንዴት ዘገባዎችን መፃፍ ይቻላል

ባህል ከሚገለጽባቸው እና ከሚተዋወቅባቸው መንገዶች አንዱ የሆነው የእይታ ጥበብ ነው፡፡ በዚህ የእይታ ጥበብ በሀገራችን የሚገኙ ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ እሴቶችን መዝግቦና ቀርጾ በማስቀረት (በማስቀመጥ) ካለፈው ትውልድ የተላለፉትን የእይታ ጥበባትና የተለያዩ የኪነ-ጥበብና የሥነ-ጥበብ ውጤቶች ከአሁኑ እና ዘመኑ ከደረሰበት ስልጣኔ ደረጃ አንጻር ጎን ለጎን በማስኬድና በማስቀመጥ የማህበረሰቡን የአኗኗር ፣ የአለባበስ ፣ እንዲሁም የቤት አሰራራቸውን ጨምሮ በተለያዩ የእይታ ጥበባትና የኪነ-ጥበብና የሥነ-ጥበብ አመዘጋገብ የማስተዋወቅ ስልት ነው፡፡ ቀርጾ በማስቀመጥ እንደ ቅርስና እንደ ታሪክ ዐውድ ከዘመን ዘመን እንዲሻገርና ትውልድ እንዲያውቀው በመማድረግ ተማሪዎችም ባህላዊ እሴትንና ታሪክን መንከባከብና መጠበቅ ብሎም መጎብኘት እንዲችሉ መማርና ማወቅ አለባቸው፡፡

***የማንቂያ ጥያቄ፡-***

1. ልጆች ከአሁን በፊት ስለጎበኙት ቦታ ቀድመው የያዙትን ማስተዋሻ በመጠቀም በዘገባ ወይም በደብዳቤ መልኩ አጭር ፅሁፍ በመፃፍ ለክፍል ጓደኞቻችውእንዲያነቡ ማድረግ፡፡

## 3.2.1. ህብረተሰባዊ ድርማዎችን በስነ-ጥበብ መቃኘት

በአካባቢያችን በርካታ ሀገረበቀል ዲራማ (ድርሰት) እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህን ሀገር በቀል ድርጊያዎችን በጥበብ በቃኙና ለተመልካች በቀርቡ ከፍተኛ አስተዋፆ አላቸው የጋሞ ማህበረሰብ የዕርቅ ስነ-ስርዓት የዱቡሻ ሰርዓት ማህበራዊ ፈያዳው ከፍተኛ ነው፡፡

**ዱቡሻ**

ዱባሻ በመባል የሚታወቁት ባህላዊ አደባባዮች የመንደሩ ልዩ የባህል እና አገር በቀል እውቀት አቅም አንዱ ነው፡፡ ዱቡሳዎች ለጋሞ የተለያዩ ማኅበራዊ እና ባህላዊ ገጽታዎቻቸውን ለመሰብሰብ እና ለማካፈል የሚገለገሉባቸው ትልቅ ቦታዎች ናቸው፡፡

የማህበረሰብ ጉዳዮችን ሆን ብለው ሰዎች ተሰብስበው የሚሰበሰቡበት ቦታ ነው፡፡ለምሳሌ ዱቡሻ በዋናነት የአንድ መንደር ነዋሪዎች ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሀገር ሽማግሌዎች የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታ ሆኖ ያገለግላል፡፡ እንዲሁም ለቅሶ ልምዶች እና ለማህበራዊ ፣ ባህላዊ ክብረ በዓላት እና ሃይማኖታዊ በዓላት ለማክበር የሚው ቦታ ነው፡፡

በጋሞ ማህበረሰብ ውስጥ ላካ ዱቡሻ በተለይ ልዩ እና በጣም የተከበረ ቦታ ነው፡፡ በዓመቱ ውስጥ የማህበረሰብ ስብሰባዎችን በተለያዩ ገጽታዎች ያስተናግዳል፡፡ እንዲሁም ከዚህም በላይ በዓመት አንድ ጊዜ በማስቀላ

ክብረ በዓልን በማሳተፍ ሁሉንም ማህበረሰብ ያስተናግዳል። ይህ ቀን በአከባቢው ማህበረሰብ ላካ ቃማ ወይም የላካ ቀን ተብሎ ይጠራል።

በዚህ ቀን ሁሉም አስራ ሁለቱ ቀበሌዎች ተሰብስበው መሲቅላን ለማክበር ተሰባስበው በጣም በሚያነቃቃ እና በሚያስደስት ሁኔታ በመጨፈር እና በመዘመር።

በተጨማሪም በዚህ ቀን የፖለቲካ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳይ የውይይት ልምዶች እንደ የበዓሉ በጣም አስፈላጊ አካል ተካትተዋል። ከዚህ አንፃር ፣ በማህበረሰቦች መካከል ግጭቶች ከተነሱ ፣ ባህላዊ የግጭት አፈታት ወይም ድርድር የሚከናወነው በዚህ ቦታ እና ቀን በመንደሩ ሽማግሌዎች ነው።ይህ የዱቡሻ ቦታ ለመንደሩ ነዋሪዎች አንድነትን ፣ ደስታን ፣ ሰላምን እና ደህንነትን ለረዥም ጊዜ እንዲጠብቁ ትልቅ ትርጉም አለው። በተጨማሪም በዚያ ቦታ የተከናወነው ባህላው እንቅስቃሴ የመንደሩን ነዋሪዎች የቆዩ ባህሎችን ፣ ደንቦችን እና ወጎችን ለቀጣይ ትውልድ በዘላቂነት ለመጠበቅ እና ለማስተላለፍ የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ። ይህ ባህላዊ አደባባዮች ቦታ ለጋሞ ሰዎች የማንነት ምንጭ ፣ መስተጋብር እና ትስስር ሆኖ በማገልገል ለመንደሮቹ ትልቅ ማኅበራዊ-ፖለቲካዊ እሴት አለው።

### 3.2.2. ሀገረሰባዊ (ሀገረ በቀል) ባህላዊ ድራማዎች

ሀገረሰብ ማለት አንድ አካባቢ የሚኑሩ ቡድኖች አምነው ተማምነው ሚከውኑት ዲርጊያዎች እምነቶች ናቸው። ባህል በጣም ጥሩ የሚባሉ ከሰው ልጆች ሁሉ አስፈላጊ ነገር ነው ግሳፅ ምክር ውገዛ መሰል ያሉበት ዲራማዊ ድረጊያዎች ያሉበት ነው።

**መልመጃ 6**

1. ሀገር በቀል ዲራማ ምንድነው?
2. ዱቡሻ ማለት ምንድነው?
3. በዱቡሻ ምን ምን ይደረጋል?

## የምዕራፍ ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ የበርካታ ባህል እና የተፈጥሮ መስህቦች ያሉባት ሀገር ናት፡፡ እነነዚህንም የባህል እና የተፈጥሮ መስህቦች በተለያዩ የሃገራችን ቦታዎች እናገኛቸዋለን፡፡

ኢትዮጵያ በዓለማችን እጅግ ጥንታዊ የስልጣኔ ታሪክ ያላት ክርስትናን እና እስልምናን፣ የዋቄፈና እምነትን ጨምሮ የበርካታ ሀይማኖት ተከታዮች በፍቅር እና በአንድነት የሚኖሩባት ድንቅ አገር ናት፡፡ በቅድመ ሰው ዘር ጥናትም የመጀመሪያ የሰው ዘር መኖሪያ /መገኛ/ ፣ ቡናን ለዓለም ያስተዋወቀች የበርካታ ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ባለቤት የሆነች አገር ናት፡፡

አገራችን በተለየ ሁኔታ የቋንቋ እና የባህል ብዝሃነት የሚታይባት ባህላዊ እና ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤዎች በኪነ-ጥበብ ፣ በስነ-ጥበብ እና በእደ-ጥበብ አዋዝታ ማራኪ ዕይታዎችን የፈጠረች አስደናቂ እና አስደማሚ አገር ናት፡፡ ለዚህም የሥልጣኔ ፣ የባህል እና የታሪክ ባለቤት ለመሆኗም ከአስራ ሁለት በላይ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ ቅርሶች በዓለም አቀፍ መድረክ በዩኔስኮ በማስመዝገብ ታላቅነቱን ያስመሰከረች ሃገር ናት፡፡ ይኸም የሰው ልጆች ሁሉ ቅርስ የሆኑ ሃብቶችን ያቀፈች የዓለማችን ድንቅ አገር ያደርጋታል፡፡

ኢትዮጵያ ከኧት እጅግ ብዙ የባህል ሀብቶቿ ውስጥ በማይዳሰሱ ቅርሶች ዘርፍ ሙዚቃው እና ውዝዋዜውን እናገኛለን፡፡ በሙዚቃ እና ውዝዋዜ እረገድ ሀገራችን ያላት አቅም ከፍተኛ እና ቀደምት ከሚባሉት የሚመደብ ነው፡፡

## የማጠቃለያ ጥያቄዎች

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ

1) ታሪካዊ ቦታዎች የምንላቸው ምን አይነት ቦታዎችን ነው?
2) የጋረዱላ ተራራ በየትኛው የኢተዮጵያ ክፍል እናገኘዋለን?
3) ታሪካዊ ቦታዎችን መጎብኘት ምን ጥቅም አለው?
4) ታሪካዊ ቦታዎችን መጠበቅ እና መንከባከብ ምን ጥቅም አለው ትላላችሁ? አስረዱ፡፡

1) ልጆች የተፈጥሮ መስህብ ናቸው የምንላቸው ምን አይነት ቦታዎችን ነው?
2) የአባያ እና የጫሞ ሀይቆች በየትኛው የኢተዮጵያ ክፍል እናገኛቸዋለን?
3) የነጭ ሳር ብሄራዊ ፓርክ የሚገኘው በየትኛው የኢተዮጵያ ክፍል እናገኘዋለን?
4) የተፈጥሮ መስህብ ያላቸውን ቦታዎች መጎብኘት ምን ጥቅም አለው?

# ምዕራፍ አራት

## 4. አድናቆት

*የክፍለ ጊዜ ብዛት = 25*

### መግቢያ

የትውንና የእይታ ጥበብ አድናቆት ሁሉንም ታላላቅ ሥነ-ጥበባት የሚለዩትን ሁለንተናዊ እና ጊዜ የማይሽራቸው ባህሪያት እውቀት እና ግንዛቤ መስጠት ማለት ነው፡፡

ሙዚቃ ፣ ዳንስ ፣ ስዕል ፣ ቲያትር እና ሲኒማ እነዚህ ጥበቦች የሰብአዊነትን ጥናት ለመረዳት የሚረዱ የትምህርት ቅርንጫፎች ናቸው፡፡ ሙዚቃ ምናልባት በትውን ጥበባት ሁለንተናዊ ሊሆን ይችላል እና በእያንዳንዱ ህብረተሰብ ውስጥ ሙዚቃ ይገኛል እንዲሁም ሥዕል የፈጠራ መግለጫ ዜይቤ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የተለያዩ ስራዎች አድናቆትን ሊያገኙ የሚችሉት የማህበረሰቡን ፣ የአካባቢውን ባህላዊ የሆኑ ይዘቶችን ይዞ በሚቀርብበት ጊዜ ነው፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ባህላዊ ገፀታዎችን የአካባቢውን መልካም ስራዎችን በማድነቅና ለሌላው አካባቢ ስለ አካባቢው እውቅና መስጠት ነው፡፡

### ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጤቶች፡-

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- ሀገረ-ሰባዊ ጥበባት ፣ ትውን እና የእይታ ጥበባት ምን እንደሆነ ይለያሉ፡፡
- በአካባቢያቸው የሚታወቁ ባህላዊ ዜማዎችን ፣ ዘፋኞችን እና ስራዎቻቸውን ለይተው ይረዳሉ፡፡

- የማህበረሰብ ሙዚቃዎች ምን እንደሚመስሉ ይረዳሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ግብዓቶች፡-**

- ምቹ የመለማመጃ ክፍል (አዳራሽ)፡፡
- የተቀረፁ ድምፆችን የሚያጫውቱ የሙዚቃ ማጫወቻ (ቴፕ ፣ ጅፓስ) ወ.ዘ.ተ
- ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያ
- ቀለማት
- ቀለም መቀቢያ (ቡሩሽ)
- ንፁህ ወረቀት
- ከትምህርቱ ጋር የተየያዙ ዜማዎች ወይም መዝሙሮች የተቀረፀበት ካሴት (ቪዲዮ)
- የተለያዮ የሙዚቃ መሣሪያዎች

**የማሰተማሪያ መንገድ፡-**

- ገለፃ
- ውይይት
- ተግባራዊ ልምምድ
- ጥያቄ እና መልስ
- በዝማሬ የማስተማር ስልት
- አስመስሎ መስራት (መተወን)

**አጠቃላይ የክትትልና ግምገማ ዘዴዎች፡-**

- የጽሑፍና የቃል ጥያቄ ፣
- በተግባር የሚከናወኑ ሥራዎች ምልከታ ፣
- የተሰሩ ሥራ ውጤቶ ምልከታ

## 4.1. ሀገረሰባዊ ጥበባት በትውን እና እይታ ጥበባት በኢተዮጵያ

*የክፍለ ጊዜ ብዛት = 25*

**መግቢያ**

ጥንታዊው ሰው በዋሻ ውስጥ ሲኖር ሕይወቱ በአንድ ላይ የተመሰረተ እንደ ነበር ጠቋሚ መረጃዎች በዋሻ ግድግዳዎች ላይ ተነድፈው የተገኙ የአዳኙ እና የታዳኙ ስዕሎች የስነ-ጥበብ /የኪነ- ጥበብ/ ውጤቶች ናቸው፡፡ የእለት ከእለት ክንዋኔዎች በግጥም ፣ በእንጉረጉሮ ፣ በትረካ ፣ በስነ-ቃል ፣ በስነ-ስዕል ፣ በስነ-ፅሑፍ  እያደገ የሄደው የስነ ጥበብ ዘርፍ ሁሉ የሚያንፀባርቁት ከእውነተኛው ሒወት በመነሳት ነው፡፡

ሀገረ-ሰባዊ እና ባህላዊ ጥበባት ሥር የሰደዱ እና የአንድን ማህበረሰብ ባህልዊ ክንዋኔዎች የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ እነሱ ከሀገረ-ሰባዊ እና ከባህላዊ ቅርስ መስኮች ጋር የተዛመደ ገላጭ ባህልን ያካትታሉ፡፡ የማይዳሰሱ የባህል ጥበቦች እንደ ሙዚቃ ፣ ባህላዊ ውዝዋዜዎች ፣ ተረት(ትረካ) ፣ ታሪካዊ ምስሎች መዋቅሮች ያሉ ቅርያችን ያካተታሉ፡፡ በኢትዮጲያ በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ሀገረ-ሰባዊ ጥበባትን በማህበረሰቡ በስራ ወቅት የጥበብ እንቅስቃሴ ግጥሙ ፣ ሙዚቃው ፣ ትያትሩ ፣ ባህላዊው ውዝዋዜው ፣ ስነ ህንፃው እነዚህን ከንውኖች በማህበረስቡ መካከል ያለው ጥሩ እና ተግባራዊ ስነ-ጥበብን ያሳየናል፡፡

### 4.1.1. ሀገረሰባዊ የሙዚቃ ጥበባትን አድናቆት መስጠት

ሀገረሰባዊ የሙዚቃ ጥበባት የምንለው በማህበረሰቡ ወይም በአካባቢው የሚታወቁ የማህበረሰቡን ባህል ፣ ወግ እና ስርዓት የያዘ የአካባቢውን ገፅታ በሚያንፀባርቅ መልኩ እና የሙዚቃ ስራዎቻቸውንም የሚገልፁት በራሳቸው ወይም አካባቢያዊ በሆኑ የሙዚቃ መሳሪያዎች ሲሆን ይህንኑ ስራዎቻቸውን ለሌላው አካባቢ ወይም ለሌላው አለም የሚያሳውቁት

ሀገረሰባዊ ጥበባትን በመጠቀም አካባቢው እውቅናን እና አድናቆትን እንዲያገኝ የደረጋሉ፡፡ ስራዎችን የሚሰሩም የማህበረሰቡን ወግ እና ባህል ጠንቅቀው በሚያውቁ እና በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች አልያም የማህበረሰቡን ባህል እና ወግ እሴቱን ጠብቀው ፣ አኗኗሩን የሚያንፀባርቁ፡፡ ትክክለኛ የባህል ሙዚቃዎች የተፃፉ ግጥሞችን በሚገባ በማዳመጥ ስለ ማህበረሰቡ ባህልና ወግ ማወቅ ይቻላል፡፡

## ከትምህርቱ የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ተምረው ካጠናቀቁ በኋላ

- ተማሪዎች በዘፈን፣በዳንስ፣ በትወና፣ በነፃ ንድፍ እና በፎቶ ግራፍ ይሳተፋሉ፡፡
- በማህበረሰባቸው አካባቢ የሚዜሙ ቀደምት የባህል ሙዚቃዎችን ምን ይመስሉ እንደነበር ይገነዘባሉ፡፡
- በአካባቢያቸው የሚታወቁ ባህላዊ ዜማዎችን ፣ ዘፋኞችን እና ስራዎቻቸውን ለይተው ይረዳሉ፡፡
- ተማሪዎች የተለያዩ ዜማዎችን በመጫወት አድናቆት ይሰጣሉ፡፡

***<u>የማነቃቂያ ጥያቄ</u>***

1. በአካባቢያችሁ በህብረተሰቡ ዘንድ በጣም ተደማጭ እና ተወዳጅ የሆነ የስራ ሙዚቃ ካለ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡላቸው?

**ፍንጭ**

1. ተደማጭና ተወዳጅ የስራ ሙዚቃ ካለ እንዲያቀርቡ አድርጓቸው?

**ጠቃሚ መረጃ**

ከላይ በመግቢያችን እንደገለፅነው የማህበረሰቡን ወግ እና ባህል የሚገልፁ ብሎም ለስራ እንዲነሳሱ ከተዜሙት ሙዚቃዎች መሃል ስለ ጋሞ ማህበረሰብ አካባቢ ሀገረሰባዊ **ያምቤ** በሚል ዕርስ በ **ደሬ የሙዚቃ ቡድን** የተሰራ የስራ ሙዚቃ(ዘፈን) ከታች የምናየው ይሆናል

**ያምቤ**

ስራ ላይ ነን እኛ ስራ ላይ ነን

ስራ ላይ ነን እኛ ስራ ላይ ነን

በስራችን ሀገርን ለማስዋብ

ወደ ሀገር ቤት ቱሪስት ለመሳብ

ተፈጥሮና ሰውን ለማስታረቅ

የህዝባችን ጤናን ለመጠበቅ

ስራ ላይ ነን ይሄው ስራ ላይ ነን

ስራ ላይ ነን እኛ ስራ ላይ ነን

ስራ ላይ ነን እኛ ልማት ላይ ነን

በወዛችን ሀገርን ለማልማት

ከሀገራችን ድህነት ለማጥፋት

ስራ ክቡር መሆኑን ለማሳየት

የፅድቅ ሀገር ኢትዮጲያን ለማየት

ስራ ላይ ነን እኛ ስራ ላይ ነን

ስራ ላይ ነን እኛ ልማት ላይ ነን

**ግጥም፡- የህዝብ እና አብረሃም ቴጋ**

**ዜማ፡- የህዝብ**



*ምስል 4.1 በጋሞ ብሄረሰብ ዴሬ የሙዚቃ ቡድን በተጫወቱት የሙዚቃ ቪዲዮ ላይ ያምቤ በሚለው የሙዚቃ ርዕስ በተሰራው የስራ ሙዚቃ የተወሰደ ምስል*



*ምስል 4.2 በጋሞ ብሄረሰብ ዴሬ የሙዚቃ ቡድን በተጫወቱት የሙዚቃ ቪዲዮ ላይ ያምቤ በሚለው የሙዚቃ ርዕስ በተሰራው የስራ ሙዚቃ የተወሰደ ምስል*

***<u>መልመጃ -4.1</u>***

1) ስለ አንድ አካባቢ ባህል ለመዝፈን በአካባቢው ውስጥ ስላሉ ተፈጥሯዊ መልክአ ምደራዊ አቀመቀመጥ ፣ ያሉ ሀብቶችን ፣ የማህበረሰቡን አኗኗር ወ.ዘ.ተ ማወቅ ተገቢ ነው ትላላችሁ? ለምን ?

***<u>የመልመጃ 4.1 መልስ</u>***

1) አዎ, ስለ አካባቢው ትክክለኛ መረጃ ለሌላው ማህበረሰብ ለማሳወቅ፡፡

## 4.1.2. ለሀገረሰባዊ ስነ-ጥበባት ማድነቅ

*የክፍለ ጊዜ ብዛት = 9*

ሐገረሰባዊ ስነ-ጥበባት ሲባል ጥበብ የራሱ የሆነ ቅርፅ ፣ እድገት ፣ ለውጥ እና መሻሻል ሲኖረው ቀደም ባለው ጊዜ ይሳሉ የነበሩ ስዕሎችን ብንመለከት የማህበረሰቡን የተለያዩ ክንዋኔዎችን ለማሳየት ከሚጠቀሙባቸው ቦታዎች የሃይማኖት ስፍራዎች ትልቁን ድረሻ ይወስዳሉ፡፡ በመሆኑም በየቤተ-መቅደሶች የሚገኙ የስነ-ጥበብ ውጤቶችን ብንመለከት የሃገረሰባዊ ስዕል አሳሳል የተላበሱ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን መንፈሳዊ ይዘት ቢኖራቸውም ክብ ፊት ፣ ትላልቅ አይኖች ያለሏቸው እና ቀለም አተቃቀማቸው ኢተዮጵያዊ መልክ መያዛቸው ሃገረሰባዊ የጥበብ አገላለፅ ዘይቤ ስላላቸው ከሌሎች የአሳሳል ዜቤዎች የተለዩ ናቸው፡፡



*ስዕል 4.2 ሐገረሰባዊ ስዕል*

## 4.1.3. *ሀገረሰባዊ ዕደ-ጥበባት*

**እደ-ጥበብ**

**እደ-ጥበብ በአካባቢችን የሚገኙ ማህበርሰቦች ለበዓላዊ እና ለባህላዊ ጠቀሜታ የሚውሉ መገልገያዎች የእደ ጥበብ የተሰሩ የፈጠራ ውጤቶች ናቸው፡፡**

**ለምሳሌ፡- የሸማ ሥራ ፣ የሸክላ ሥራ ፣ የእንጨት ሥራ ፣ የብረታብረት ሥራ ወዘተ…፡፡ የመሳሰሉት ማህበርሰቡ ለየእለት ኑሮው መገልገያ የሚጠቀምባቸው እና የገቢ ሚንጭ ከማግኘታቸው ባሻገር የካባቢቸውን ዕደጥበብ አሠራራቸው ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር የሚያገናኛቸው በመሆኑ**

አንደኛው ማህበረሰብ የሌላውን ማህበረሰብ የጥበብን ውበት በማድነቅ የጥበብ ውጤቶችን ይጋራሉ፡፡

ለምሳሌ፡- የሽማ ሥራ በጋሞ በአካባቢ ከሚተገበሩ የእደ-ጥበብ ዓይነቶች አንዱ ሲሆን በአካባቢያችን ማህበረሰቦች እና ሌሎች በኢትዮጵያ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች ለበዓላት ፣ ለአዘቦት ግዚያት በመልበስ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡



*ስዕል 4.3 የእደ-ጥበብ ውጤት ከሆኑት ጥቂቶቹ የሽማ ሥራ አልባሳት*

**የሸክላ ስራ**

የሸክላ ሥራም በአካባቢያችን ከሚተገበሩ የእደ-ጥበብ ዓይነቶች አንዱ ሲሆን ይህኛው የጥበብ ዓይነት የሚከናወነው ባካባቢያችን ከሚገኝ የሸክላ አፈር በሸክላ ባለሙያዎች ይሠራል፡፡

ለምሳሌ፡- የመመገቢያና የመጠጫ ፣ የማብሰያ ቁሳቁሶች አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገዉ ይሠራሉ፡፡




*ስዕል 4.4: የእደጥበብ ውጤቶች ከሆኑት የሸክላ ሥራ ዓነቶች ጥቂቶቹ*

## የእንጨት ሥራ

የእንጨት ሥራም እንደሌሎች የዕደ-ጥበብ አይነቶች በእንጨት ሥራ ባለሙያዎች የሚከናወን የሥራ ዓይነት ነው፡፡ የዚህ ሥራ ውጤቶች በአብዛኛው ለቤት ውስጥ መገልገያ ይዉላሉ፡፡

ለምሳሌ፡- አልጋ ፣ ጠረጴዛ ፣ ወንበር (መቀመጫ) ፣ ቁምሳጥን (የልብስ ማስቀመጫ) ፣ ቁምሳጥን (የእቃ ማስቀመጫ) ፣ ሙቀጫ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡



ስዕል 4.5: ከእንጨት የተሠሩ የቤትውስጥ መገልገያዎች

### መልመጃ 2

1. ሀገረሰባዊ ጥበብ የምንላቸው ምንድናቸው?
2. የዕደ-ጥበብ ውጤቶችን በዝርዝር ጻፉ?

## ማጠቃለያ

ጥንታዊ ሰው በዋሻ ውስጥ ሲኖር ሕይወቱ በአንድ ላይ የተመሰረተ እንደነበር ጠቋሚ መረጃዎች በዋሻ ግድግዳዎች ላይ ተነድፈው የተገኙ የአዳኙ እና የታዳኙ ስዕሎች የስነ-ጥበብ /የኪነ-ጥበብ/ ውጤቶች ናቸው፡፡ የእለት ከእለት ክንዋኔዎች በትውን ፣ በግጥም ፣ በእንጉረጉሮ ፣ በትረካ ፣ በስነ-ቃል ፣ በስነ-ስዕል ፣ በስነ-ፅሑፍ እያደገ የሄደው የስነ ጥበብ ዘርፍ ሁሉ የሚያንፀባርቁት ከእውነተኛው ሒወት በመነሳት ነው፡፡ ስለዚህም ነው ኪነ-ጥበብ የአንድ ሐገር ህብረተሰብ ባህል እና ወግ እሴት ትስስር የአንድነት እና የልዩነት አርማ ተደርጎ የሚታየው፡፡ የገሀዱ አለምን ድረጊት በአዲሰ ሒወት በመተካት ከሸኖ እና አስውቦ የሚያቀርበው ከያኒ ደግሞ የህዝብ ሀብት ነው፡፡ ታሪክ ሰሪ ቢሞትም ታሪክ እንደማያልፈው ሁሉ የጥበብ ሰው ቢያልፍም ጥበቡ አያልፍም፡፡ ለጥበብ ስራው ህያውነት ግን የሃብቱ ባለቤት የሆነው ህብረተሰብ ተቆርቋሪነት ወሳኝ ነው፡፡

ሀገረሰባዊ የዕይታ ጥበባት ስንል በአካባቢያችን የሚገኙ የማህበረሰቡን ባህልና ውግ እሴታዊ ትውፊቶች የሚንጸባርቁበት ዕደ-ጥበባዊና ሥነ-ጥበባዊ በማህበረሰቡ የተሰሩ የፈጠራ ውጤቶች ማለትም ስዕሎች ፣ ቅርጻቅርጾች ፣ የሸመናና የሸክላ ሥራዎች ለሎችም ኢትዮጵያዊ ሥነ-ውበትን የተላበሱ በመሆናቸው ኢትዮጵያን ባላት የእይታዊና ሌሎች ጥበባት ተደናቂና የተለየች ያደርጋታል፡፡

አገረሰባዊ ጥበባት የምንላቸው በአካባቢችንና በሌሎችም የሀገራችን ክፍሎች በተለያዩ የእደ-ጥበብና የእይታ-ጥበብ ባለሞያዎች የሚተገበር የጥበብ ውጤት ነው፡፡

ሀገረሰባዊ የሙዚቃ ጥበባት የምንለው በማህበረሰቡ ወይም በአካባቢው የሚታወቁ የማህበረሰቡን ባህል ፣ ወግ እና ስርዓት የያዘ የአካባቢውን ገፅታ በሚያንፀባርቅ መልኩ እና የሙዚቃ ስራዎቻቸውንም የሚገልፁት በራሳቸው ወይም አካባቢያዊ በሆኑ የሙዚቃ መሣሪያዎች ሲሆን ይንኑ ስራዎቻቸውን ለሌላው አካባቢ ወይም ለሌላው አለም የሚያሳውቁት ሀገረሰባዊ ጥበባትን በመጠቀም አካባቢው እውቅናን እና አድናቆትን እንዲያገኝ ያደረጋሉ፡፡ ስራዎችን የሚሰሩም የማህበረሰቡን ወግ እና ባህል ጠንቅቀው በሚያውቁ እና በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች አልያም የማህበረሰቡን ባህል እና ወግ እሴቱን ጠብቀው ፣ አኗኗሩን የሚያንፀባርቁ ትክክለኛ የባህል ሙዚቃዎች የተፃፉ ግጥሞችን በሚገባ በማዳመጥ ስለ ማህበረሰቡ ባህልና ወግ ማወቅ ይቻላል፡፡

እደ-ጥበብ በአካባቢያችን የሚገኙ ማህበርሰቦች ለበዓላዊ እና ለባህላዊ ጠቀሜታ የሚውሉ መገልገያዎች የእደ-ጥበብ የተሰሩ የፈጠራ ውጠቶች ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡- የሸማ ሥራ ፣ የሸክላ ሥራ ፣ የእንጨት ሥራ ፣ የብረታብረት ሥራ ወዘተ…፡፡ የመሳሰሉት ማህበርሰቡ ለየእለት ኑሮው መገልገያ የሚጠቀምባቸው እና የገቢ ምንጭ ከማግኘታቸው ባሻገር ያአካባቢያቸውን ዕደ-ጥበብ አሠራራቸው ከሌሎች ማህበረሰቦች ጋር የሚያገናኛቸው በመሆኑ አንደኛው ማህበረሰብ የሌላውን ማህበረሰብ የጥበብን ውበት በማድነቅ የጥበብ ውጤቶችን ይጋራሉ፡፡

የሸክላ ሥራም በአካባቢያችን ከሚተገበሩ የእደ- ጥበብ ዓይነቶች አንዱ ሲሆን ይህኛውየጥበብ ዓይነትየሚከናወነው ባካባቢያችን ከሚገኝ የሸክላ አፈር በሸክላ ባለሙያዎች ይሠራል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ለሚከተሉ ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነው መልስ ምረጥ

1. ከሚከተሉት ውስጥ የእደጥበብ ውጤት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የሸመና ስራ

ሐ. የሸመና ሥራ

ለ. የቤትአሠራር

መ. ሁሉም

2. ከሚከተሉት ውስጥ ሸክላ ሠራ ውጤት የሆነው የቱነው?

ሀ. እንስራ

ሐ. ወንበር

ለ. ሙቀጫ

መ. ሁሉም

3. ከሚከተሉት ውስጥ የሸመናስራ ውጤትየሆነው የቱነው?

ሀ. ሙቀጫ

ሐ. ጠረጴዛ

ለ. እንስራ

መ. ጋቢ

4. ሀገረሰባዊ ጥበብ የምንላቸው እነማናቸው?

ሀ. ዕደ-ጥበብ እና የእይታ-ጥበብ

ሐ. ኪነ-ሕንጻ

ለ. ሥነ-ጥበብ

መ. ሁሉም

5. ከሚከተሉት ውስጥ ከእንጨት ሥራ ውጤት ያለሆነው የቱነው?

ሀ. አልጋ

ሐ. ወንበር

ለ. ከሰል ማንደጃ

መ. ሁሉም

6. ያምቤ ሙዚቃ መልክቱ ስለምንድነው

ሀ. የሰርግ

ለ. የስራ

ሐ. የለቅሶ                                         መ. ሁሉም

**የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ**

1/ መ/ሁሉም

2/ ሀ/እንስራ

3/ መ/ ጋቢ

4/ መ/ሁሉም

5/ ለ/ከሰል ማንደጃ

6/ለ/የስራ

# ምዕራፍ አምስት

## 5. የቡድን ተግባር (ግኑኝነት፤ተግባቦት እና ተግባር)

*የክፍለ ጊዜ ብዛት = 20*

### መግቢያ

የትውንና የእይታ ጥበባት ወደ ተሻለ የአዕምሮ እድገት የሚመራ ፣ የሰውን ግንኙነት የሚጨምር ፣ ደረጃን የሚያሻሽል ፣ ማህበራዊነትን የሚረዳ ፣ አልፎ ተርፎም የጭንቀት ደረጃን ስለሚቀንስ የትውንና የእይታ ጥበባት በትምህርት ቤቶች ውስጥ በጣም ወሳኝ ርዕሰ ጉዳይ ነው።

የሙዚቃ ትምህርት በልጆች የቋንቋ ችሎታን ያሻሽላል ያዳብራል። ሙዚቃ አንጎልን ያነቃቃል ፣ እና በተለያዩ ድምፆችና ግጥሞች ፣ ተማሪዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ የቃላት ዝርዝር በቀላሉ ይይዛሉ። ሙዚቃ ለሌሎች ቋንቋዎች መረዳትን ይሰጣል ፣ ይህም ለተማሪዎች በተለየ ቋንቋ የመረዳትና የመግባባት ችሎታ መሰረት ይፈጥራል።

የትውን እና የእይታ ጥበባትን ለልጆች ማስተማር ያስፈለገበት አይነተኛው እና ዋነኛው ምክንያት እነዚህ የትውን እና የእይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያላቸው ቅርበት ነው።

የትውን እና የእይታ ጥበባት ትምህርት የልጆችን የሙዚቃ ፣ የትያትር ፣ የውዝዋዜ እና የስዕል ክህሎት ከማዳበሩም ባለፈ በሌሎች የትምህርት አይነቶች የሒሳብ ክህሎታቸውን ፣ የቋንቋ /የማንበብ እና የመፃፍ/ ክህሎታቸውን ፣ የሳይንስ ክህሎታቸውን ፣ ማህበራዊ ሳይንስ /የእርስ

በእርስ ግንኙነታቸውን/ ፣ የታሪክ እውቀታቸውን ወ.ዘ.ተ… ለማዳበር አይነተኛ እና ምርጫ የማይገኝለት ነው፡፡

ሙዚቃ ከፍተኛ የማስታዎስ ችሎታን ያዳብራል፡፡ በሚስቡ ዜማዎችና በተለያዩ ድምፆች አማካኝነት ሙዚቃ ከእኛ ጋር የሚቆራኝበት መንገድ አለው ሙዚቃ በአግባቡ ጥቅም ላይ ሲውል ለመማር ማስተማር ሁነኛ መሣሪያ ነው፡፡

**ከምዕራፉ የሚጠበቁ ውጥቶች**

- ተማሪዎች በጋራ እና በቡድን ሆነው ስለ ተፈጥሮ ስለ ቀለማት ያዜማሉ ይወዛወዛሉ፡፡
- ተማሪዎች ስለ ወንዞቻች ፣ ሐይቆቻች ፣ አዕዋፋት ፣ ከዋክብት ወ.ዘ.ተ ያዜማሉ፡፡

**ማነቃቂያ ጥያቄ**

1. ተማሪዎች ስለ ሙዚቃ ፣ ድራማ እና ስዕል ለመምህራችሁ አብራሩ?

ፍንጭ

1. ተማሪዎች ስለ ሙዚቃ ፣ ድራማ እና ስዕል እንዲያብራሩ እድል ስጧቸው፡፡

## 5.1. የትውን እና እይታ ጥበባት እርስ በእርስ ያላቸው ግኑኝነት

*የክፍለ ጊዜ ብዛት = 20*

የትውን እና የእይታ ጥበባት የምንላቸው ሙዚቃ ፣ ስዕል ፣ ትያትር እነዚህ እርስ በርስ የሚያገናኛቸው በጣም በርካታ ነጥቦች ይገኛሉ፡፡

የትውንና የእይታ ጥበባት ሰው ድምፃቸውንና አካላት መልእክት ወይም የስነ ጥበብ መግለጫን የሚያስተላልፉበት የጥበብ ዓይነት ነው፡፡ የእይታ ጥበቦች በእይታ መንገዶች፡፡ ለምሳሌ፡- ፎቶግራፍ ፣ ስዕል ፣ ቅርፃቅርፅን በእይታ ጥበብ ውስጥ የሚያስተላልፉበት መንገድ ነው፡፡

የትውን ጥበባት እንደ ቲያትር ፣ የህዝብ ንግግር ፣ ዳንስ ፣ ሙዚቃ እና ሌሎችም በመሳሰሉት በትውን አማካኝነት ስራቸውንና ስሜታቸውን የሚገልፁባቸው መንገዶች አሏቸው፡፡ የትውን ጥበባት ባህላዊ ታሪኮችን በዳንስና ከረጅም ጊዜ በፊት በመድረክ ላይ ትዕይንቶችን በመገንባት ማሳየት ይችላሉ፡፡ እናም በዚህ መልኩ የትውንና የእይታ ጥበባት እርስ በርሳቸው የሚገናኙ ናቸው፡፡

የትውንና የእይታ ጥበቦች እንዲሁ እርስ በርስ ይደጋገፋሉ፡፡ የእይታ ጥበባት ፣ ድራማ እና ሙዚቃ በሲኒማግራፊ መልክ ሲጣመሩ ፣ ለምሳሌ ለማሳወቅ እና ለማሳመን የኪነጥበብ ኃይሉ እየጠነከረ ይሄዳል፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች የሚሰሩትን ዶክመንተሪ ፊልሞች ብንመለከት የአካባቢውን መልዕክቶችን በድራማ ለማሳየት ፣ የእይታ ምስሎችን እና የሙዚቃ አጃቢዎችን ይጠቀማል፡፡

ስነ-ጥበቡን በመጠቀም ዘጋቢ ፊልሞቹ መረጃዉን በበለጠ በሚያስተጋቡ መንገዶች ለማስተላለፍ በተመልካቾቹ ስሜት ላይ ጉልህ ሚናን ይጫወታል፡፡

## 5.1.1. የትውን እና እይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ግኑኝነት

የትውንና የእይታ ጥበባት ከሌሎች ትምህርት ዓነቶች ጋር ያለው ግንኙነት በተፈጥሮ ሳይንስ ፣ በማህበረሰብ ሳይንስ ፣ አከባቢ ሳይንስ ፣

በቋንቋ እና በሌሎችም የትምህርት ዘርፎች የእይታ-ጥበብ የየትምህርቱ ምስላዊ (ሥዕላዊ) ገላጭ በመሆን የትምህርቱ መርጃ መሣሪያ ከመሆኑም ባሻገር ጠቃሚና አጋዥ መረጃን ከመስጠት በተጨማሪ ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ እንዲረዱ ያደርጋል፡፡

### 5.1.2. ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማዛመድ

ሙዚቃን ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር ልናገናኝ እንችላለን፡፡ ከሁሉም በፊት ተማሪዎች ወደ ክፍላቸው እንደገቡ አእምሯቸው እንዲነቃቃ ሙዚቃን መጫወት ይመከራል፡፡ እንዲሁም ደግሞ ተማሪዎች የሙዚቃን ግጥሞች ቶሎ የመያዝና ያለመርሳት አቅም ስላላቸው የተለያዩ የትምህርት ዓይኖችን በሙዚቃ ማስተማሩ ይመረጣል ለምሳሌ ለአካባቢ ሳይንስ ትምህርት ስለ አካባቢ ፅዳት ፣ ስለ እፅዋት እና ስለተለያዩ አካባቢ ሳይንስ ትምህርትን ስለሚያካትቱ እርዕሶች በሙዚቃ በሚገባ ማስተማር ይቻላል፡፡ ሌላው የትምህርት ዓይነት ደግሞ ሂሳብ በሂሳብ ትምህርት ተማሪዎች በቀላሉ ስለ ሂሳብ ስሌቶች ስለ መደመር ፣ መቀነስ ፣ ማካፈል እና ማባዛት በሙዚቃ ቢማሩ የተሸለ የመረዳት አቅም ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም ስለ ስነ-ህይወት ተማሪዎች ስለ ግል ንፅህናቸው ፣ እና ስለ ሰውነት ክፍላቸው በሙዚቃ ሲማሩ በተሸለ ሁኔታ ስለ ትምህርቱ ይረዳሉ፡፡ እናም ለተማሪዎች ከላይ በጠቀስናቸው የትምህርት ዓይነቶች እና ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ሙዚቃን በማካተት ትምህርታቸውን እንዲረዱ ማድረግ ይመረጣል፡፡

## መዝሙር 1

### የስሜት ህዋሳት

ማነው የሚያውቅ አምስቱን የስሜት ህዋሳት

ማነው የሚያውቅ አምስቱን የስሜት ህዋሳት

ዓይን፣አፍንጫ፣ጆሮ፣ምላስ እና እጅ ናቸው

ዓይን አፍንጫ ጆሮ ምላስ እና እጅ ናቸው

ማነው የሚያውቅ ጥቅማቸውን የስሜት ህዋሳት

ማነው የሚያውቅ ጥቅማቸውን የስሜት ህዋሳት

በዓይናችን እናያለን በአፍንጫችን እናሸታለን

በጆሯችን እንሰማለን በምላሳችን እንቀምሳለን

በእጃችን እንዳስሳለን ነገሮችን እንለያለን

## መዝሙር 2

### መማር እወዳለው

ትምህርት ቤት መሄድ እኔ እወዳለው

ተማሪ ነኝ እኔ መማር እወዳለው

መምህሬን እሰማለው መምህሬን እሰማለው

ጎበዝ ስለሆንኩኝ ሁሌ አጠናለው

ማጥናት እወዳለው ማጥናት እወዳለው

ከጥናት በኋላ እኔ እጫወታለው

መጫወት እወዳለው መጫወት እወዳለው

እናትና አባቴን በስራ አግዛለው

እናቴን እወዳለው አባቴን አወዳለው

ታላቅ የሚለኝን እኔ እሰማለው

**መልመጅ 5.2**

- ሙዚቃን ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማዛመድ ለክፍል ጓደኞቻችሁ እና ለመምህራችሁ አቅርቡላቸው

**የመልመጃ 5.2 ፍንጭ**

- ተማሪዎች ሙዚቃን ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር በማዛመድ እንዲዘምሩ እድል ስጧቸው

**ማነቃቂያ ጥያቄ**

- ተማሪዎች ለክፍል ጓደኞቻችሁ የምታውቁትን ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር የተዛመዱ ሙዚቃዎችን አቅርቡላቸው

**ፍንጭ**

- ተማሪዎች ሙዚቃን ከተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ጋር ለምሳሌ ከአካባቢ ሳይንስ ጋር፣ከሂሳብ ትምህርት ጋር እና ወ.ዘ.ተ ትምህርት አይነቶች ጋር እያዛመዱ እንዲዘምሩ አድርጓቸው

ሙዚቃ ሃሳባችንን እና ስሜታችንን ከመግለፅ ባለፈ ሌሎች የትምህርት አይነቶችንም ለመማር ያግዘናል፡፡

# ማጠቃለያ

የትውን እና የእይታ ጥበባት ትምህርት የልጆችን የሙዚቃ፣ የትያትር፣ የውዝዋዜ እና የስዕል ክህሎት ከማዳበሩም ባለፈ በሌሎች የትምህርት አይነቶች የሒሳብ ክህሎታቸውን፣ የቋንቋ /የማንበብ እና የመፃፍ/ ክህሎታቸውን፣ የሳይንስ ክህሎታቸውን፣ ማህበራዊ ሳይንስ /የእረስ በእረስ ግንኙነታቸውን/ ፣ የታሪክ እውቀታቸውን ወ.ዘ.ተ ለማዳበር አይነተኛ እና ምርጫ የማይገኝለት ነው፡፡

ሙዚቃ ልጆች ደስተኛ ሆነው እና እየተዝናኑ በጥሩ የመማር ፍላጎት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ያግዛቸዋል፡፡ ሙዚቃ የረጅም ጊዜ የማስታዎስ አቅምን የሚጨምር በመሆኑ ልጆች በሙዚቃ የተማሩትን ትምህርት በቀላሉ ለማስታዎስ ያስችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ከፍ ለማድረግ እና የመማር ማስተማሩን ሂደት ተማሪዎች እንዲወዱት ለማድረግ ሌሎች የትምህርት አይነቶችንም በሙዚቃ ማስተማር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው የተለያዩ የዘረፉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

ሙዚቃ ሃሳባችንን እና ስሜታችንን ከመግለፅ ባለፈ ሌሎች የትምህርት አይነቶችንም ለመማር ያግዘናል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተክክለኛውን መልስ ምረጡ

1. የእይታ ጥበብ የምቆራኛቸው የትምህርት ዓይነቶች አነማንናቸው

   ሀ/የተፈጥሮ ሳይንስ ለ/ማህበራዊ ሳይንስ ሐ/ቋንቋ መ/ሁሉም

2-የሙዚቃ ጥበብ ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ፋይዳው ምንድነው

   ሀ/ምንም አይገናኝም ለ/በስእልና በምስል ይገለጻል ሐ/ በሙዚቃ እንድንረዳ ይጠቅማል  መ/ ሀ እና ለ መልስ ናቸው፡፡

3-የእይታ ጥበብ ስእልን በምንምን ይወክላል

ሀ/በንድፍ  ለ/በቀለም ቅብ  ሐ/በቀርጻቀርጽና ህትመት መ/ሁሉም

1-ከሚከተሉት ውስጥ የእይታጥበብን አይገልጽም

- ለ/ስእል መሳል ሐ/ቀለምቅብ መስራት መ/ፎቶማነሳት

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ሀሰት በማለት መልሱ

1-የእይታ ጥበብ ለሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ምንም ግኑኝነት የለውም

2-በአካባቢያችን የሚገኙ አበባዎችሁሉም ቀለማቸው አንድዓይነት ነው

3-የእይታ ጥበብ፤ የተወና ጠበብ ፤ ሙዚቃ ከሁሉም ትምህርቶችጋር ይቆራኛል

4-የትውን ጥበብ በሌሎች የትምህርት አርፎች በድራማ መልክ ይገለጻል

5-ሙዚቃን ከየትኛውም የትምህርት ዓይነት ጋር ልናዛምድ እንችላለን

### -የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች መልስ

#### -ምርጫ

1-መ/ሁሉም

2-ሐ

3-መ/ሁሉም

4-ሀ/መኪና ማሽከርከር

**-እውነት ሀሰት**

1- ሀሰት

2-ሀሰት

3-እውነት

4-እውነት

5-እውነት

# ዋቢ መፅሐፍት


- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ1ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ2ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ3ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ የተዘጋጀ የ4ኛ ክፍል የኤስቴቲክስ ማስተማሪያ መጽሐፍ 1998 ዓ.ም.